# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 240 ሚያዝያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## ነጻ የንግድ ቀጣናው ተጠቃሚዎች ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ያስችላል

ገጽ 4


ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




ፎቶ፡- በረከት ታደሰ

## «ውሃ ውስጥ የሚገኘው የብረት ማዕድን መብዛቱ የከተማዋን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፈታኝ አድርጎታል»

- ኢንጂነር ፊልታሞ ዲብሎ

**ሙሉቀን ታደገና ሞገስ ተስፋ**

ቦንጋ፡- በውሃ ጉድጓዶች ውስጥ የሚገኘው የማዕድን መጠን መብዛቱ የቦንጋ ከተማን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፈታኝ እንዳደረገው የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ኢንጂነር ፊልታሞ ዲብሎ ገለጹ።

በቢሮው የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ዘርፍ ምክትል ኃላፊ ኢንጂነር ፊልታሞ ዲብሎ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳመለከቱት፤ የቦንጋ

«ውሃ ውስጥ የሚገኘው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ከ815 ቶን በላይ የሻይ ቅጠል ምርት ወደውጭ ተልኳል

- የ200 ሚሊዮን ዶላር የቡና ግብይት ኮንትራት ተፈርሟል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት 815 ነጥብ ስድስት ቶን የሻይ ቅጠል ምርት ለውጭ ገበያ መቅረቡን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አስታወቀ። በየካቲት ወር በተደረገው የቡና ኤግዚቢሽን የውጭ ሀገር

ከ815 ቶን በላይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ጥራት ስብራትን ለመጠገን የሚያስችል አሠራር ቀርጾ ወደ ሥራ ገብቷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በትምህርት ጥራት ላይ የሚስተዋለውን ስብራት ለመቅረፍ የበኩሉን ጥረት እያደረገ መሆኑን የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ። የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ብርሀነመስቀል ጠና (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በትምህርት ጥራት ላይ የሚስተዋለውን ስብራት ለመቅረፍ ፍኖተ ካርታና የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ገብቷል።

ኢትዮጵያ ላለፉት 100 ዓመታት አንድም የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ሳይኖራት ትምህርትን ስትመራ የኖረች ሀገር ናት ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ አዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ እንደሚያስፈልግ አመላክቷል። በዚህም ለውጡን ተከትሎ እንደገና ከተደራጁ ተቋማት አንዱ የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ነው ብለዋል።

በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ከ800 ሺህ በላይ መምህራን አሉ ያሉት ዶክተር ብርሀነመስቀል፤ በዩኒቨርሲቲ ውስጥም 40 ሺህ የሚደርሱ መምህራን ይገኛሉ። ይህን ሁሉ መምህር ይዘን

ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ብርሀነመስቀል ጠና (ዶ/ር)


ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565



አቶ ደረጀ ተግይበሉ

# ሕገ ወጥ ስደትን ለመከላከል ሁሉን አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እየተሠራ ነው

## - 49 ሺ 491 ተመላሾች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ሕገ ወጥ ስደትን ለመከላከል ሁሉን አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን አጠናክሮ እየሰራ መሆኑን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። ለ49 ሺ 491 ከስደት ተመላሾች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል።

በሚኒስቴሩ የሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተሟላ የዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደረጀ ተግይበሉ ለኢፕድ እንዳስታወቁት በተለይም፣ ለሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ተብለው ለሚታሰቡ የኅብረሰተብ ክፍሎች መደበኛ በሆነ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ እየሰጠ ይገኛል።

ሥራ አስፈጻሚው እንደገለጹት፤ በመደበኛ መልኩ ከሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ በተጨማሪ፣ በርካታ ታዋቂ ሰዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች የሃይማኖት አባቶችና የፖለቲካ ሰዎች የሚሳተፉባቸው ንቅናቄዎችም በየጊዜው ይካሄዳሉ።

በግንዛቤ ማስጨበጫው በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍልሰት ጋር የተያያዙ ነባራዊ ሁኔታዎች ምን ይመስላሉ? መደበኛ ያልሆነ ስደት ምን ዓይነት ጉዳት ያስከትላል በሚሉ ጉዳዮች ላይ ወጣቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

የአዘዋዋሪዎቹ ሁኔታ ምን እንደሚመስል፣ ስደተኞች በመዳረሻ ሀገራት ምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚገጥማቸውና ስደት የሚያስከትለው አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳትን የሚያስረዳ ግንዛቤ ይሰጣል።

በሕገ ወጥ ፍልሰት ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ እድሜያቸው ከ14 እስከ 17 ያሉ ሕፃናትም ጭምር እንደሚጓዙ አቶ ደረጀ ያነሱ ሲሆን፤ የግንዛቤ ማስጨበጫው ሁሉን አቀፍ እንዲሆን ጥረት እንደሚደረግም ነው ያነሱት።

እርሳቸው እንዳሉት፣ በጎ ነገር ነው ብሎ በማሰብ ቤተሰብ ንብረቱን ሸጦ አንዳንዱም ከብድርና ቁጠባ ተበድሮ ልጆቹን ወደ ስደት ይልካል።

በሃይማኖት አባቶችም ዘንድ ልጆችን መርቆ ለስደት የመሸኘት ልምድ አለ። የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች በሚሰሩበት ጊዜም እነዚህን ነባራዊ ሁኔታዎች ታሳቢ ባደረገ መልኩ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎችም ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚሰራው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በተጨማሪ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ስደተኞችን ወደ ሀገራቸው የመመለስ ሥራም ይሠራል።

ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበርም ተመላሾቹ በምርጫቸው ስልጠና እንዲያገኙ ከማድረግ ጀምሮ፣ የሥራ ዕድልና መነሻ ካፒታል እንዲያገኙ የማድረግ ሥራዎችንም እየሰራ ይገኛል።

በዚህም፣ ካለፈው 2015 በጀት ዓመት ጀምሮ እስከ 2016 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ 148 ሺ ዜጎች መካከል ለ49 ሺ 491 ያህሉ የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል።

ሚኒስቴሩ፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር በሀገር ውስጥ ባሉ አማራጮች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ እገዛ ካደረገላቸው ዜጎች በተጨማሪ በራሳቸው መንገድ የራሳቸውን ገቢ መፍጠር የቻሉ ተመላሾች መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

# የስታርት አፕ ሥነ-ምህዳርን ምቹ ለማድረግ የድጋፍ ማዕቀፍ ያስፈልጋል

**ዳግማዊት አበበ**



በለጠ ሞላ (ዶ/ር)



ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- የስታርት አፕ ሥነ-ምህዳርን ምቹ ለማድረግ የድጋፍ ማዕቀፍ ያስፈልጋል ሲል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ2016 በጀት ዓመት የ9 ወራት እቅድ አፈጻጸሙን ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በትናንትናው እለት አቅርቧል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ሪፖርቱን ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ በቴክኖሎጂ፣ በምርምር፣ በዲጂታል ኢኮኖሚ አቅም ግንባታ እና መሰረተ ልማት ግንባታ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ሚኒስትሩ፤ ሀገራዊ የኢኖቬሽን፣ የቴክኖሎጂና የምርምር አቅሞችን ከማጎልበት አኳያ ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸው፤ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የኢኖቬሽን መሠረተ ልማት አቅሞችን መለየትና መረጃዎችን የማደራጀት ሥራዎችን በመሥራት በዘርፉ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ሚኒስቴሩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የፈጠራ ሀብት ያላቸውን የስታርት አፕ ሃሳቦችን በማወዳደርና ድጋፍ በማድረግ ከዘርፉ የሚገኙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን እንዲሁም የሥራ ዕድልን ለማሳደግ እየተሠራ ቢሆንም እንደ ሀገር የስታርት አፕ ፖሊሲ የለም። የስታርት አፕ ስነ-ምህዳርን ለማስፋት የድጋፍ ማዕቀፍ ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት በሦስት ደረጃ ባሉ ስታርት አፖች ማለትም በቅድመ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ እና በሦስተኛ ደረጃ ስታርትአፖች አንድ ሺህ 491 የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል ብለዋል።

ሀገራዊ የዲጅታል ኢኮኖሚ ልማትን ከማሳደግም ሆነ ችግር ፈቺ የምርምር ውጤቶችን ወደ ሥራ በማስገባት ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለዲጂታል ኢኮኖሚ ወሳኝ የሆኑ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች መከናወናቸውን ያነሱት ሚኒስትሩ፤ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት ወደ ማህበረሰቡ እንዲደርሱ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እቅዱን የጋራ በማድረግና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመገምገም የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ ችሏል።

ሚኒስቴሩ ተጠቃሚ የሚያደርጉና ችግር ፈቺ የምርምር ሥራዎችን መሥራቱ፣ የስፔስና ጆስፓሻል መረጃዎችን ለሀገር ልማት እንዲውል ማድረጉ እንዲሁም የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓትን በመዘርጋትና ምቹ ከባቢ በመፍጠር የተሠሩ ሥራዎች በጥንካሬ የሚነሱ ናቸው ብለዋል።

እንደ ሰብሳቢው ገለጻ፤ ሚኒስቴሩ ያከናወናቸው ሰፊ ሥራዎች ቢኖሩም በቀጣይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ያለባቸው ጉዳዮች አሉ። በተለይም የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን እውን ለማድረግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችና የተገኙ ውጤቶች በየጊዜው መግለጽና ከባለድርሻ አካላት ጋርም በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል።

ስታርት አፖችን ከማልማት፣ ከመደገፍ ባለፈ በክልሎች ማዕከላትን በመክፈት ፈጣሪ ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ሕዝቡ ቴክኖሎጂውን አውቆ መጠቀም እንዲችል ከትምህርት ቤቶች ጀምሮ ዲጂታል ላይ ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ገልጸው፤ የጎለበተ የስታርት አፖችን ከማልማትና ውጤታማ ከማድረግ አንጻር በክልሎች የሚሠሩ ሥራዎች ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

# ሴቶችን በኢኮኖሚ ለማብቃት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል

**ቃልኪዳን አሳዬ**




ወይዘሮ ነፃነት ዳባ ድጋፉን አስረክበዋል፤

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ሴቶችን በኢኮኖሚ ለማብቃት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ የሴቶች ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አስታወቀ።

ቢሮው ሰሞኑን ከሁሉም ክፍለ ከተሞች ለተመለመሉ በቂ የገቢ ምንጭ ለሌላቸው አንድ ሺህ 51 ሴቶች ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የተስማሚ ቴክኖሎጂዎች ድጋፍ አድርጓል።

በዚሁ ወቅት የቢሮው የሴቶች ዘርፍ ምክትል ኃላፊ ነፃነት ዳባ፤ የተደረገው ድጋፍም የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ችግር በመፍታት ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ያለመ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሮ ነፃነት ገለጻ፤ ድጋፉ እናቶችንና የሚያስተዳድሯቸውን ቤተሰቦች በተለያየ መልኩ ተጠቃሚ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ሲሆን፤ የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ገቢ የሚያገኙበትን እድል የሚፈጥር ነው።

ባለፉት ጊዜያትም የባንክ ደብተር እንዲከፍቱ በማድረግ ለሥራ መነሻ የሚሆን ገንዘብ እንዲቆጥቡ ሲደረግ መቆየቱን አስታውሰው፤ ድጋፉ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ መቆየቱንና እስካሁን ባለው ጊዜ ከ5ሺህ በላይ ሴቶች ተጠቃሚ መሆን መቻላቸውን ጠቁመዋል።

ግብዓቱ በቂ ሳይሆን ለሥራ ማስጀመሪያ እንደሚሆን ያነሱት ወይዘሮ ነፃነት፤ የዚህን ዓመት ድጋፍ ለየት የሚያደረገው በማህበር ተደራጅቶ ለመሥራት አስቸጋሪ የሆነባቸውን ሴቶች ያቀፈና ከአኗኗራቸው ጋር ተስማሚ መሆኑ ነው ብለዋል።

ቴክኖሎጂዎቹ የሴቶችን ልፋት የሚቀንሱና ወጪ ቆጣቢ ናቸው። በቀጣይም ሴቶቹ በማህበር ተደራጅተው ለመሥራት የሚያስችሉ ናቸው ያሉት ኃላፊዋ፤ በተሰጡ ቁሳቁሶች ተጠቅመው በቀላሉ በመኖሪያ ቤታቸው መሥራት የሚችሉ በመሆኑ ከልጆቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው እንዳይርቁ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

ከዚህ ቀደም ድጋፉን ያገኙ ሴቶች በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት ከራሳቸው አልፈው ለሌሎችም የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል ያሉት ደግሞ በቢሮው የሴቶችን ተሳትፎ ማብቃትና ተጠቃሚነት ዳይሬክተር ወይዘሮ ስፍራሽ አልማው ናቸው።

አሁን ላይ የተሰጠው ድጋፍም የተሰራውን ጥናት መነሻ በማድረግ እንደሆነ የገለጹት ወይዘሮ ስፍራሽ፤ ቢሮው እስከ ወረዳ ድረስ ባለው መዋቅር የክትትልና ቁጥጥር ሥራ እንደሚሠራና ሴቶቹ ባገኙት ድጋፍም ወደሥራ የማይገቡ ከሆነ የራሱን እርምጃ እንደሚወስድ ጠቁመዋል።

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ በቀጣይ ሴቶቹ ሥራዎቻቸውን የማስፋት ፍላጎት አላቸው። የብድር ችግር እንዳይገጥማቸው ከስኬት ባንክና ከየኛ ማይክሮ ፋይናንስ ጋር የተጀመረው የብድር ማመቻቸት ተግባር በየካ፣ በለሚኩራና በአራዳ ክፍለ ከተሞች እየተከናወነ ነው። ይህ ተግባር በቀጣይ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተጠናክሮ ይቀጥላል።

የድጋፉ ተጠቃሚ የሆኑት ወይዘሮ አለምነሽ ተሾመ በበኩላቸው፤ ድጋፉን በማግኘታቸው እጅግ ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸው፤ በግል ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው እንደሚሰሩና የሚያገኙት ገቢ ሁለት ልጆቻቸውን ለማስተዳደር አነስተኛ እንደሆነ ተናግረዋል።

ወይዘሮ አለምነሽ አክለውም ባገኙት ድጋፍ የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት የቤተሰባቸውን ህይወት ለመቀየር ዝግጁ እንደሆኑ ጠቁመዋል።

ድጋፉ የእንጀራ፣ የዳቦ መጋገሪያ በቀላሉ ከቦታ ወደቦታ በማንቀሳቀስ የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስችሉ ማሽኖች የተካተቱበት ነው።

ዜና



# በፀጥታ ችግሮች ሳቢያ የደም አሰባሰብ በከተሞች ተወስኗል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ አካባቢዎች ባሉ የፀጥታ ችግሮች ሳቢያ የደም አሰባሰብ ሂደት በከተማ መወሰኑን የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ። የአቅርቦት ችግሩን ለመቅረፍ ከተቋማት ጋር እየተሠራ መሆኑም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎትና ቀይ መስቀል ማህበር በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ትናንት ተፈራርመዋል።

የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አሸናፊ ታዘበው እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ባሉት የፀጥታ ችግሮች ሳቢያ የደም አሰባሰብ ሂደት በከተማ ተወስኗል።

በሀገሪቱ ያሉ የፀጥታ ችግሮች የደም አቅርቦት ማነስን ማስከተሉን ጠቁመው፤ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ግንቦት ስምንት ቀን 2016 ዓ.ም የሚቆይ የደም ማሰባሰብ ንቅናቄ እንደሚካሄድና በሁሉም ክልሎች በሚገኙ የቀይ መስቀል ማህበርና በ48 የደም ባንክ ቅርንጫፎች ላይ ደም እንደሚሰበሰብ አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር የደም አገልግሎትን ለዘመናት ሲሰጥ ቆይቷል ያሉት ዶክተር አሸናፊ፤ የጋራ መግባቢያ ሰነዱ ሁለቱ ሰብአዊ ተቋማት በሕይወት አድን ሥራ በመቀራረብ ለመሥራት የሚያስችላቸው መሆኑን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ምክትል ፀሐፊ አቶ አበራ ሉሌሳ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ንቅናቄ በመፍጠር የሚፈለገውን የደም መጠን ለማሰባሰብ የሚያስችል ነው።

ማህበሩ ላለፉት 89 ዓመታት በርካታ ሰብዓዊ አገልግሎቶችን ሲሰጥ መቆየቱን የገለጹት አቶ አበራ፤ በተለይም የደም ባንክ አገልግሎትን ለ42 ዓመታት ሲመራ ቆይቷል ብለዋል።

የደም አቅርቦት ሕይወት የማዳን ሥራ በመሆኑ ከማህበሩ ዓላማ ጋር በቀጥታ ግንኙነት እንዳለው ጠቅሰው፤ ማህበሩ በሰው ሰራሽ፣ ተፈጥሮ አደጋዎችና በጸጥታ ችግር ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ እንደሚሠራ አስረድተዋል።

የቀይ መስቀል ማህበር በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ200 ሺህ በላይ በጎ ፈቃደኞች እንዳሉት ገልጸው፤ የደም ማሰባሰብ ሂደት ሕይወት የማዳን ተግባር በመሆኑ በሁሉም ቅርንጫፎች ተግባራዊ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማህበር በዓልን ምክንያት በማድረግ ከነገ ጀምሮ እስከ ግንቦት ስምንት "ደስታን እለግሳለሁ ደስታውም ሽልማቴ ነው"በሚል መሪ ሃሳብ ደም የማሰባሰብ ሥነ ሥርዓት እንደሚካሄድም ተገልጿል።

# «56 በመቶው የጨቅላ ሕፃናት ሞት የሚከሰተው በጤና ተቋማት የንጽህና ጉድለት ነው»

- የጤና ሚኒስትር መቅደስ ዳባ (ዶ/ር)

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በታዳጊ ሀገራት 56 በመቶው የጨቅላ ሕፃናት ሞት የሚከሰተው በጤና ተቋማት የንጽህና ጉድለት ነው ሲሉ የጤና ሚኒስትር መቅደስ ዳባ (ዶ/ር) ገለጹ። የ"ጽዱ ኢትዮጵያ" ንቅናቄ አካል የሆነው የጽዱ ጤና ተቋማት ንቅናቄ መርሀ-ግብር በአለርትና በቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ትናንት ተጀምሯል።

የጤና ሚኒስትር መቅደስ ዳባ (ዶ/ር) በንቅናቄው ማስጀመሪያ ወቅት እንደተናገሩት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ አብዛኛው የጨቅላ ሕፃናት ሞት የሚከሰተው ከተቋማት ንጽህና ጉድለት ነው።

እ.አ.አ. በ2019 በተደረገ ጥናት በተለይ በታዳጊ ሀገራት ከጨቅላ ሕፃናት ሞት 56 በመቶ የሚሆነው የሚከሰተው በተቋማት ንጽህና ጉድለት መሆኑን ጠቁመዋል። በሀገራችን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ችግሩን በተወሰነ መልኩ መቅረፍ ቢቻልም አሁንም ተጨማሪ ስራዎች የሚፈልግ ጉዳይ ነው ብለዋል።

ጨቅላ ሕፃናት ተገቢውን እንክብካቤና የጤና ክትትል አግኝተው ማደግ እንዳለባቸው የገለጹት ሚኒስትሯ፤ ለዚህም የጤና ተቋማት የተሻለ ጥራትና ደረጃ እንዲኖራቸው መስራት እንደሚገባ አመላክተዋል።

የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ መርሀ-ግብር ሀገሪቱ ብቁና ጤናማ ዜጋ ለመፍጠር የያዘችውን ግብ እውን ለማድረግ የሚረዳ መሆኑንም ዶክተር መቅደስ አስረድተዋል።

ዶክተር መቅደስ እንደገለጹት፤ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተጀመረው ሀገር አቀፍ ንቅናቄ የጽዱ ኢትዮጵያ አካል ነው። ንቅናቄው በክልሎች በማጠናከር እንደሀገር በዘርፉ ዓለም ከደረሰች ለመድረስ በቁርጠኝነት መሥራት ያስፈልጋል።

የተጀመረው ንቅናቄ ከግብ ለማድረስም የአንድ ሴክተር ብቻ ኃላፊነት ባለመሆኑ ሁሉም በቁርጠኝነት መስራት እንዳለበት አሳስበዋል።

የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ ከማህበራዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ሁለንተናዊ እድገት ማስመዝገብ የሚቻልበት መሆኑን አመላክተዋል።



ፎቶ፦ ሐዲስ አብርሃ

የጽዱ ጤና ተቋማት ንቅናቄ መርሀ-ግብር ተጀምሯል

ንቅናቄው ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመቀነስ ከፍተኛ ሚና አለው ያሉት ዶክተር መቅደስ፤ በተለይ በኢትዮጵያ እየጨመረ የመጣውን ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቁጥር ለመቀነስ ትልቅ ግብዓት እንደሚሆን አስረድተዋል።

የአለርት እስፔሻላይዝድ ኮንፕሬንሲቭ ሆስፒታል ዋና ሥራ አስኪያጅ ሽመልስ ገዛኸኝ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ንቅናቄው በጤናው ዘርፍ ለማሳካት የታቀደው ውጤት ከግብ ለመድረስ የሚያግዝ ነው ብለዋል።

በሆስፒታሉ 118 የውስጥና ስድስት የጋራ መገልገያ መጸዳጃ ቤቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በንቅናቄው የሆስፒታሉ የፍሳሽ ሥርዓት ማሻሻል፣ዲውቲ ሩሞች የማደስ፣ የአካባቢ ጽዳት ዘመቻ፣ የሻወርና መጸዳጃ ቤት ግንባታና እድሳት እንዲሁም ታካሚዎች ማቆያ ቦታ ማስፋፊያ ተግባራዊ እንደሚደረጉ ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ሽመልስ ገለጻ፤ በሆስፒታሉ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ12 ሺህ በላይ የቀዶ ሕክምናና 11 ሺህ 500 ተኝተው ለሚታከሙ ህሙማን አገልግሎት ተሰጥቷል። በተጨማሪም በተመላላሽ ህክምና በቀን ከሁለት ሺህ 700 በላይ አገልግሎት እየተሰጠ እንደሆነ አብራርተዋል።

ዶክተር ሽመልስ አክለውም፤ ከዚህ ጎን ለጎን እንደ ሀገር የታቀደው የዲጂታል ኢትዮጵያ በሆስፒታሉ ተግባራዊነት የሚያረጋግጡ ሥራዎች በትኩረት እንደሚሰሩ አስረድተዋል።

የንቅናቄው ፕሮግራም ከማስጀመር ጎን ለጎን የጽዱ ጤና ተቋማት እድሳት፣ የመጸዳጃ ቤት ግንባታ፣ የጽዳት ስራዎች ማስጀመርና ለአቅመ ደካሞች የተገነቡ ሦስት መኖሪያ ቤቶች ማስረከብ ፕሮግራም ተካሂዷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) "ጽዱ ኢትዮጵያ" የሚል ስያሜ የተሰጠው አዲስ ተግባርና ንቅናቄ ይፋ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው።

# ስልጠናው የደንብ ማስከበር አባላት የአገልጋይነት ስሜት እንዲላበሱ የሚያስችል ነው

**አማን ረሺድ**

ሠንዳፋ፡- ለደንብ ማስከበር አባላት እየተሰጠ ያለው ስልጠና የአገልጋይነት ስሜት እንዲላበሱና ተልዕኳቸውን በብቃት እንዲፈጽሙ የሚያስችል መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን አስታወቀ።

በመዲናዋ የሚታየውን ሕገ-ወጥነት ለመቆጣጠር የሚረዳ የአቅም ግንባታ ስልጠና በትናትናው ዕለት በኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ መስጠት ተጀምሯል።

የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ስልጠናው የደንብ ማስከበር አባላት በአዲስ አበባ ከተማ የሚታየውን ደንብ መተላለፍ ቁጥጥር ሥራ የአገልጋይነት ስሜት ተላብሰው ተልዕኳቸውን በብቃት እንዲፈጽሙ የሚያስችል ነው።

የደንብ ማስከበር አባላት ሀገራቸውን መውደድ ይኖርባቸዋል ያሉት ሻለቃ ዘሪሁን፤ ሰልጣኞች በሚኖራቸው የስልጠና ቆይታ ስለ ሀገር ወዳድነት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ የሚያጎለብቱበት እንዲሁም በቂ ትምህርት የሚያገኙበት ነው ብለዋል።

ሥራቸውን በሚከውኑበት ወቅት በተለይ ሥነ-ምግባር ጋር በተገናኘ የአገልጋይነት ስሜት እንዲላበሱና በከተማ ውስጥ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የደንብ መተላለፎችን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ እውቀት የሚቀስሙበት መሆኑን ገልጸዋል።

በአቅም ግንባታ ስልጠናው አምስት ሺህ ነባር ኦፊሰሮች የሚሳተፉ ሲሆን፤ በአምስት ዙር ከአንድ ወር በላይ ጊዜ እንደሚቆይ ሻለቃ ዘሪሁን ጠቁመዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ከተማዋን ለነዋሪው ምቹና ጽዱ



ለማድረግ ከኮሪደር ልማት በተጨማሪ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ አውስተው፤ ባለስልጣኑም የልማት ሥራዎቹ በተያዘላቸው እንዲጠናቀቁ ኃላፊነቱን እየተወጣ ነው ብለዋል።

አባላቶቹ ለረጅም ጊዜ ሳይሰለጥኑ መቆየታቸውን ጠቅሰው፤ ባለስልጣኑ በተሻለ መንገድ ሕዝብን ለማገልገልና ውጤታማ እንዲሆን ስልጠና መስጠቱ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ አጫጭርና ረጅም ስልጠናዎችን የሚሠጥ ስመ ገናና ዩኒቨርሲቲ መሆኑን ገልጸው፤ ሰልጣኞች በተለይ በከተማዋ በሚገኙ አደባባዮችና መንገዶች ላይ የሚደረጉ ሕገ ወጥ ንግዶች፣ ሕገ ውጥ የቤት ግንባታና መሬት ወረራ ላይ ውጤታማ የቁጥጥር ሥራ መሥራት የሚችሉ ብቁ ኃይል ሆነው እንደሚወጡ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ምክትል ኮምሽነር ጀነራል መስፍን አበበ በበኩላቸው፤ ሰልጣኞች በዩኒቨርሲቲው የሚወስዱት ስልጠና የፖሊስ ተልዕኮን ለማሳካት የሚያግዝ መሆኑን ገልጸዋል።

ሰልጣኞች በሚኖራቸው አጭር የስልጠና ጊዜ ለሚሰሯቸው ተግባራት ወሳኝ እውቀት እንዲያገኙ በቂ ዝግጅት ማድረጉን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም የደንብ ማስከበር አባላት የተሻለ የአካልና የአእምሮ ቁመና እንዲኖራቸው የሚያግዝ ስልጠና እንደሚሰጣቸው ተናግረዋል።

ዩኒቨርሲቲው በምሥራቅ አፍሪካ ብቸኛ የፖሊስ ማሰልጠኛ መሆኑን ጠቁመው፤ ከምስረታው ጀምሮ በርካታ መደበኛ የፖሊስ አባላትን ማፍራት ችሏል ብለዋል።

# ነጻ የንግድ ቀጣናው ተጠቃሚዎች ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ያስችላል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ተጠቃሚው ማኅበረሰብ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ ያስችላል ሲል የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

"የኩባንያዎች ዝግጁነት ለአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና" በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የተዘጋጀ የፓናል ውይይት ትናንት ተካሂዷል፡፡

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የዓለም አቀፍና ቀጣናዊ ንግድ ትስስር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታገሰ ሙሉጌታ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ነጻ የንግድ ቀጣናው የውጭ እና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ከመሳብ ባሻገር ተጠቃሚው ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ ያግዛል፡፡

ነጻ የንግድ ቀጣናው በነጋዴዎች መካከል ፍትሐዊ ውድድርን በማጠናከር በተመጣጣኝ ዋጋ ጥራት ያለው ምርት እንዲቀርብ ተጨማሪ አቅም ይሆናል ያሉት አቶ ታገሰ፤ ኅብረተሰቡም በነጻ የንግድ ቀጣናው ትግበራ ተጠቃሚ ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

መሪ ሥራ አስፈጻሚው እንዳመላከቱት፤ ነጻ የንግድ ቀጣናው ስምምነት በሁለት ምዕራፍ የሚደረግ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ የነበሩ የስምምነቱ ክፍሎች ተጠናቀዋል፡፡

ሙሉ ለሙሉ ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ የምርት ስሪት ሀገር ምንጭን ተመርኩዞ መከናወን ያለባቸው ስምምነቶች በቀጣይ መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡ በዚህ ረገድ 92 በመቶ የሚሆኑ ምርቶች የምርት ስሪት ሀገሮች የተበየነላቸው ሲሆን፤ በጨርቃጨርቅ እና በአውቶሞቲቭ ዘርፎች ላይ እንደአህጉር ከስምምነት ለመድረስ እየተሰራ መሆኑን አንስተዋል፡፡

በሁለቱ ዘርፎች አሠራር ዘርግቶ ከመሥራት አኳያ የሚቀሩ ሥራዎች እንዳሉ የገለጹት አቶ ታገሰ፤ ኢትዮጵያ በሁለቱም ምዕራፍ በሚደረጉ ስምምነቶች በንቃት እየተሳተፈች መሆኑን አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የታሪፍ አመዳደብና ስሪት ሀገራት አወሳሰን ዳይሬክተር አቶ ካሳዬ አየለ በበኩላቸው እንደገለጹት ፤ ኢትዮጵያ በዋነኛነት ለአህጉሩ ሀገራት የምታቀርባቸው ዕቃዎች የታሪፍ ምጣኔን በተመለከተ ዝርዝር ሰነድ ለአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ጽህፈት ቤት ጸድቋል፡፡

የጸደቀውን የታሪፍ ዝርዝር ደንብ በጋዜጣ የማሳተም ኃላፊነት የገንዘብ ሚኒስቴር በመሆኑ በአሁኑ ወቅት የታሪፍ ዝርዝሩ በገንዘብ ሚኒስቴር ይገኛል ያሉት አቶ ካሳዬ፤ ሥራው ሲጠናቀቅ በጉምሩክ ሲስተም ላይ ይጫናል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አንድ ሀገር በነጻ የንግድ ቀጣናው ምርቱን አቅርቦ ለመነገድ በቅድሚያ ምርቱ የእራሱ ሀገር ስሪት ሊሆን ይገባል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ምርቱ ሲላክ የላኪው ሀገር ስሪት መሆኑን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ካልተላከ የታሪፍ ቅነሳ አይደረግም ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ጉምሩክ ኮምሽኑ የስሪት መረጃ ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ ተሳትፎ ያደረገ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ በኩል የሚቀርቡ ምርቶች ላይ ስሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማሳተም እንዲሁም ከሌሎች ሀገራት የሚመጡ ምርቶችንም በዝርዝር ለመለየት የሚያስችል ሥራ እያከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

# «ውሃ ውስጥ የሚገኘው ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከተማን ሕዝብ የንጹህ መጠጥ ውሃ ጥያቄ ለመመለስ ከፍተኛ ውሃ መያዝ የሚችሉ አራት ጉድጓዶች በሶስት ምዕራፍ ተቆፍረው ነበር። ይሁንና በጉድጓዶቹ ውስጥ ለመጠጥ አገልግሎት የሚውል ውሃ መያዝ ካለበት በላይ የብረት ማዕድን ተገኝቷል።

የብረት መጠኑን ለመቀነስ ለበርካታ ዓመታት ከፌዴራል ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እንዲሁም ከተለያዩ የውጭ ድርጅቶች ጋር ቢሰራም ችግሩን መቅረፍ አልተቻለም ብለዋል።በዚህም እስካሁን ድረስ የቦንጋ ከተማን የውሃ አቅርቦት ጥያቄ በሚፈለገው ደረጃ መመለስ እንዳልተቻለ አስታውቀዋል።

የቦንጋ ከተማ የንጹህ መጠጥ ውሃ ችግር ለረጅም ጊዜያት የቆየ ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃለፊው፤ ቢሮው ከተቋቋመ ጀምሮ ችግሩን ለመፍታት ከአጭር ፣ ከመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ አውጥቶ በሶስት ምዕራፎች የሚተገበር ሥራ እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።

ከተማዋ የክልሉ መንግሥት መቀመጫ ከሆነች ወዲህ ከሚጠበቀው ሕዝብ በላይ ወደ ከተማዋ እየገባ መሆኑን ጠቁመው፤ ለዚህ ደግሞ የሕዝቡን ቁጥር የሚመጥን የውሃ አቅርቦት ያስፈልጋል ብለዋል። አሁን ላይ በአካባቢው የሚገኙ የውሃ ተቋማት በከተማዋ የሚገኘውን ሕዝብ የውሃ ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ማሟላት እንደማይችሉ አስረድተዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ከረጅም ጊዜ ዕቅድ አንጻር በፌዴራል ዲዛይን እና ኮንስትራክሽን ሱፐር ቪዥን ጥናት እየተጠና መሆኑን አመላክተዋል።

ከአጭር ጊዜ መፍትሔ አንጻር ደግሞ በ2016 ዓ.ም 70 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለአገልግሎት ማዋላቸውንና በዚህም 13 ሺህ 200 የከተማዋ ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

በከተማዋ ዙሪያ የሚገኙ ወንዞችን በመጥለፍ የከተማዋን የንጹህ መጠጥ ውሃ ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ከዚህ በፊት ከነበረበት 31 በመቶ በዚህ ዓመት 42 በመቶ ለማድረስ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረገ መሆኑን ኢንጂነር ፊልታሞ አስታውቀዋል።

# ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ጥራት ስብራትን ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ስለትምህርት ውድቀት ማውራት በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው ሲሉም ተናግረዋል። ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው ትውልድ የሚገነቡ መምህራንን ለማፍራት በትኩረት እየሠራ ነው።

ዩኒቨርሲቲው በዳይሬክተር የሚመሩ አምስት ማእከላትን መክፈቱን ጠቅሰው፤ ከእነዚህ ማዕከላት አንዱ በማስተማር ሙያ ላይ ለተሰማሩ ዜጎች የሥራ ላይ ስልጠና የሚሰጥ ነው። ይህም መምህር ሳይሆኑ የሚያስተምሩትን መምህር ማድረግን ያለመ ነው።

በተለይ በግል የትምህርት ተቋማት ከሚያስተምሩ መምህራን አብዛኞቹ የመምህርነት ስልጠና ያልወሰዱ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ይህ ደግሞ በሕፃናት የነገ ሕይወትና በሀገርም ላይ ትልቅ አደጋ የሚያስከትል ነው። በመሆኑም ይህን ችግር ለመቅረፍ የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት የሚያስችል ማዕከል ከፍተናል ብለዋል።

መምህርነት አማራጭ ሲታጣ የሚገባባት ሳይሆን፤ መከበር አለበት ትልቅ ሙያ ነው ያሉት ፐሬዚዳንቱ፤ በየትኛውም የትምህርት መስክ የሰለጠነ ሰው ድንገት ተነስቶ መምህር መሆን የለበትም። ከሰለጠነበት ሙያ ባለፈ የማስተማር ፍላጎት ካለውም ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ እንዴት ማስተማር እንዳለበት መሰልጠን አለበት ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው በየዓመቱ የሚቀበለው ከ600 እስከ 700 የሚደርሱ ተማሪዎችን እንደሆነ ያስታወቁት ፕሬዚዳንቱ፤ ተማሪዎችን ትምህርት ሚኒስቴር ይመድብለታል፤ ዩኒቨርሲቲውም ማስታወቂያ አውጥቶ በመምህርነት ሙያ ለመሰልጠን ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ይቀበላል ሲሉም አስረድተዋል።

ከዚህ በላይ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች ለመቀበል የዶርሚተሪ/ማደሪያ ስፍራ/ እጥረት እንቅፋት እንደሆነበት አንስተው፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 17 ሺህ ሄክታር ቦታ ማበርከቱንም ጠቁመዋል። ዛሬ ካልተዘራ ነገ ስለማይታጨድ አይሲቲን ጨምሮ የሌሎችም መሠረተ ልማቶችን ችግር ለመቅረፍ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለዩኒቨርሲቲው አስፈላጊውን ትኩረትና እገዛ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያ ትምህርት መሠረታዊ ችግር የሚስተዋለውን ስብራት በጥናት ላይ ተመስርቶ ከመፍታት ይልቅ በጨበጣ ለመቅረፍ የሚደረጉ ጥረቶች ናቸው ያሉት ዶክተር ብርሀነመስቀል፤ የሚደረጉ ጥናቶችም በለጋሽ ድርጅቶች ላይ የተንጠለጠሉ በመሆናቸው የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ያስገቡ አልነበሩም። ከዚህ ይልቅ በሌላ ሀገር የተደረጉ ጥናቶች የስም ለውጥ ብቻ ተደርጎባቸው ለኢትዮጵያ እንደተሠሩ ተደርገው የሚቀርቡበት ሁኔታም አጋጥሟል ብለዋል።

መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ዩኒቨርሲቲው ሀገር በቀል እውቀቶችን መሠረት ያደረገና በእኛ ሙያተኞች የተሠራ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀቱን ጠቁመው፤ ሀገራዊ ችግርን መሠረት ያደረገና ሀገራዊ ራዕይ የሰነቀ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድም መዘጋጀቱን አብራርተዋል።

ብቁ መምህራንን ለማፍራት ከሚያከናውነው ሥራ ጎን ለጎን ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናትና ምርምሮችን እያከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ በድሀ ሕዝብ ገንዘብ የሚሠሩ ጥናቶች ደግሞ መሬት ወርዶ ችግር የሚፈታ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

በዚህ ዓመትም ከሚያከናውናቸው በርካታ ጥናትና ምርምሮች መካከል የኢትዮጵያን ትምህርት ችግር ማዕከል ያደረጉ አራት ትልልቅ ጉዳዮች ላይ ጥናት እያደረገ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በዚህም በርካታ እንከኖችን ለመቅረፍ ትልቅ ሚና ይጫወታል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

የትምህርት ጥራት በተወሰኑ አካላት ጥረት ብቻ ሊረጋገጥ አይችልም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የሀገሪቱን የትምህርት ስብራት ለመጠገን ሁሉም ባለድርሻዎች የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

# ከ815 ቶን በላይ የሻይ ቅጠል ምርት ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ገዢዎች የኢትዮጵያን ቡና ለመውሰድ የ200 ሚሊዮን ዶላር የግብይት ኮንትራት መፈራረማቸውን ባለስልጣኑ ገልጿል።

የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ኡመር በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወራት 815 ነጥብ ስድስት ቶን በአግባቡ የተዘጋጀ የሻይ ቅጠል ምርት ለውጭ ገበያ በመላክ አንድ ነጥብ 67 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል።

የተላከው የሻይ ምርት ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ204 ቶን ብልጫ እንዳለው አስታውሰው፤ በሻይ ምርት ላይ የተሰማሩት ባለሀብቶች ውስን በመሆናቸው አሁን ላይ በዋናነት ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ እና ጉመሮ ሻይ ቅጠል ምርቱን እያቀረቡ ይገኛሉ ሲሉ አስረድተዋል።

በጋምቤላ ክልል የሚገኘው የሻይ ኢንዱስትሪ እስካሁን ወደተግባር አለመግባቱንና ምርቱ በስፋት ለማምረት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሻይ ቅጠል ልማት ላይ ክልሎች በስፋት እንዲሰሩ ኮሚቴ ተዋቅሮ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠው እየተሰራ ይገኛል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተለይ በኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉባቡር እና ቡኖ በደሌ ላይ በስፋት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።


በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አርሶ አደሮች የሻይ ቅጠል ምርት በስፋት እንዲያመርቱ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በተያያዘ በዘንድሮ ዓመት በየካቲት ወር በተደረገው የቡና ኤግዚቢሽን አንድ ሺህ የውጭ ሀገር የቡና ገዢዎች መሳተፋቸውን አስታውቀው፤ ከአሜሪካ፣ ከአውሮፓ እና ከተለያዩ ሀገራት የመጡ ቡና ገዢዎች በኤግዚቢሽኑ ተገኝተው ከኢትዮጵያ ቡና አቅራቢዎች ጋር ግብይት መፈጸማቸውን አስታውቀዋል።

በወቅቱ የኢትዮጵያን ቡና ለመግዛት የሚያስችል የ200 ሚሊዮን ዶላር የቡና ምርት ግብይት ኮንትራት ስምምነት መፈጸሙን አቶ ሻፊ አስረድቷል።

የቡና ኤግዚቢሽኑ የሀገሪቱን የቡና አመራረት ሂደት፤ ባህልና ሌሎች በቡና ዘርፍ የሚገኙ እሴቶችን ለማስተዋወቅ መዘጋጀቱን ያስታወሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ የውጭ ሀገር የቡና ገዢዎቹ ከአቅራቢዎቹ ጋር በቅንጅት እስከ ቡና ማሳ ድረስ ሄደው እንዲጎበኙ መደረጉን ተናግረዋል።

በቀጣይ ኢትዮጵያ በልዩነት የምትታወቅባቸውን የቡና ምርት ዝርያዎች በማስፋት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሰራ መሆኑን አመላክተዋል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በራስ ገዝ አስተዳደር እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት የሚበረታቱ ናቸው!

ትምህርት የዕድገት መሰረት ነው:: ለትምህርት ትኩረት የሰጡ ሀገራት በእድገት ማማ ላይ በመራመድ የዜጎቻቸውን ህይወት መቀየር ሲችሉ በአንጻሩ የትምህርት ሥርዓታቸው ደካማ የሆኑ ሀገራት የድህነትና ኋላቀርነት መገለጫ ለመሆን በቅተዋል:: ድህነት፣ ግጭት፣ ጦርነት፣ስደት፣ረሃብና የመሳሰሉት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከትምህርት ውድቀት ጋር የሚያያዙ የኋላቀርነት መገለጫዎች ናቸው::

ትምህርት በኢትዮጵያ ከአንድ ክፍለ-ዘመን በላይ የዘለለ ታሪክ ቢኖረውም በየዘመናቱ በቂ ትኩረት ባለማግኘቱ ወይም ደግሞ የየሥርዓቱ የፖለቲካ መሳሪያ ሆኖ በመዝለቁ ለሀገር ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ተስኖት ቆይቷል:: በተለይም የትምህርት ሥርዓቱ ከፖለቲካ ጥገኝነት የተላቀቀ አለመሆኑ የትምህርት ዘርፉ ሙያዊ ግዴታውን እንዳይወጣ አድርጎታል::

በተለይም በዘመነ ኢህአዴግ ለፖለቲካ ፍጆታ ብቻ ዩኒቨርሲቲዎችን እንደ አሸን በየቦታው የማቋቋሙ ተግባር የትምህርት ሥርዓቱንም ሀገሪቱንም በርካታ ዋጋ አስከፍሏቸዋል:: በዘመኑ የነበረው የትምህርት ፖሊሲ ከጥራት ይልቅ ለብዛት ትኩረት ይሰጥ ስለነበረ ተማሪዎች በቂ ዕውቀት ሳይጨብጡ ጭምር ወደ ቀጣይ ክፍል እንዲያልፉ ሲደረግ ቆይቷል::

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ደረጃውን የማይመጥኑ ተማሪዎችና ሰልጣኞችም ከመብዛታቸውም ባሻገር ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲወጡ በገበያ የማይፈለጉና በሰለጠኑበት የሙያ መስክ የራሳቸውን ሥራ እንኳን መፍጠር የማይችሉ ዜጎች እንዲበራከቱ አድርጓል:: በዚህ ሂደት ውስጥ አልፈው የሚቀጠሩ ምሩቃንም ብዙውን ጊዜ ባላቸው ብቃት የማይተማመኑ እንዲሁም የዕውቀት እና ክህሎት ችግር የሚታይባቸው ይሆናሉ:: ለመልካም አስተዳደርና ለብልሹ አሰራርም ምክንያት ሆነው ይገኛሉ::

ይህንኑ ችግር ከስር ከመሰረቱ ለመቀየር ከለውጡ ወዲህ አዲስ ፍኖተ ካርታ ተቀርጾና በሂደትም አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተነድፎ ወደ ሥራ ተገብቷል:: ከእነዚህ ለውጦች መካከል ደግሞ በፖለቲካ ተሸብበው የነበሩትን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነጻ ማውጣት እና አስተዳደራዊ ነጻነታቸውን ማወጅ አንዱ ነው::

የትምህርት ሥርዓቱ ይዞ ከመጣቸው ትሩፋቶች መካከል የዩኒቨርሲቲዎች የራስ ገዝነት መብት ነው:: አንድ ተቋም ተቋማዊ ነጻነት ተጎናጽፏል ወይም ራስ ገዝ ሆኗል ብለን ስናስብ በዋናነት ከአካዳሚና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ነጻነት ኖሯቸው ይህንንም ከተጠያቂነት ጋር በመያዝ የተሻለና ውጤታማ ሥራን እንዲሠሩ የማስቻል ጅምር ነው፡

ይህ መሆኑ ደግሞ የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአጭር ጊዜ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት ያስችላል:: ዩኒቨርሲቲዎች ተልዕኳቸው ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ፣ ተወዳዳሪና ብቁ ችሎታ ያላቸው ምሩቃንን ለማፍራትና ጥራት ያለው የምርምር ውጤት እንዲሠሩ ያስችላቸዋል::

ዩኒቨርሲቲዎች ችግር የሚያባብሱ ሳይሆን በሰላም መኖርን፣ ዴሞክራሲን፣ የሚሰብኩ ተቋማት እንዲሆኑ በተለይ ሀገር በቀል እውቀቶችን በምርምር ማወቅ፣ ለችግሮች የመፍትሔ ሃሳብ ማመንጨት፣ የዓለምንና የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት ቀጣይ አቅጣጫን ለማመላከትም ነጻነትና ራስ ገዝነት ያስፈልጋቸዋል::

ትምህርት ሚኒስቴር በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አስር የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ ለማድረግ እቅድ ይዟል። በዚህ ዕቅድ ውስጥ ከተካተቱት መካከልም ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ ሀዋሳ፣ አርባ ምንጭ እና መቐለ ዩኒቨርሲቲዎች ይገኙበታል።

ከተቋቋመ ሰባ ሁለተኛ ዓመቱን የያዘው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ የ"ራስ ገዝ" አስተዳደርን ተግባራዊ በማድረግ የመጀመሪያው ሆኗል:: በዚህ ረገድ ዩኒቨርሲቲው ከወዲሁ እያሳየ ያለው ለውጥ የሚያበረታታ ነው:: በተለይም ዩኒቨርሲቲው ለዘመናት ቅሬታ ሲቀርብበት የነበረውን የሬጅስትራር አሠራሩን ማዘመኑ የነጻነቱ ውጤት ተደርጎ የሚወሰድ ነው::

የዩኒቨርሲቲው የሬጅስትራር አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ወደ ኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ተሸጋግሯል:: ቀድሞ እንግልት ይታይበት የነበረው የክፍያና የምዝገባ ሙሉ ለሙሉ ከወረቀት ተላቆ በዲጂታል ሥርዓት ውስጥ ገብቷል::

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው የራስ ገዝ አስተዳደሩ በፈጠረለት ምቹ ሁኔታ የአሠራር ሥርዓቱን እያሻሻለ ከመምጣቱም ባሻገር ሌሎች ራስ ገዝ ለመሆን በሂደት ላይ ለሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችም አርአያ የሚሆን ተግባር እየፈጸመ በመሆኑ ዕውቅና ሊሰጠው ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።።

## ሃሳብን በነፃነት መግለፅ እስከ ምን ድረስ?

ቦጋለ አበበ

ማህበራዊ ሚዲያ ለብዙዎች የነጻ ንግግር መብታቸው እንዲከበር ያደረገውን ያህል በዚያኑ ልክ የብዙዎቹ ድብቅ አሉታዊ ባህሪ ጎልቶ እንዲወጣም አድርጎታል:: ከሁሉ በላይ ግን ጎልቶ እንዲወጣ ያደረገው በሁላችንም ውስጥ የተደበቀውን አምባገነንነት ባህሪ ነው:: ይህን ለማለት ለረጅም ጊዜ የማህበራዊ ሚዲያ ውይይታችንን ማስተዋል በቂ ነው::

እኔ ምደግፈውን ካልደገፍክ፣ የምቃወመውን ካልተቃወምክ ብሎ የሚበሻሸቀው ሰው ቁጥር አንድና ሁለት አይደለም:: በማህበራዊ ሚዲያው ላይ የሚስተዋለው በብሔር፣ ሃይማኖትንና ማንነት ላይ መሰረት ያደረገ የስድብና እና የእርግማን አይነት እጅን በአፍ እንደሚያስጭን ማንም የሚያውቀው ሀቅ ነው:: መቃወም መብት ነው:: በመቃወም እና በመሳደብ መካከል ግን ሰፊ ልዩነት አለ:: የብዙዎች ተቃውሞ ሳይሆን ስድብ ነው::

ስድቡ ደግሞ አጸያፊ ከመሆኑ የተነሳ ይሄ ስድብ ሃይማኖተኛ ነው ከሚባል ህዝብ የሚወጣ አይመስልም:: ያሳፍራል:: የበለጠ አሳፋሪው ነገር ደግሞ አንድን ሰው ሆን ብሎ ለመጉዳት ቤተሰብ ላይ ሳይቀር የሚወርደው ስድብ ዘግናኝ መሆኑ ነው:: የሞተ ዘመድ አዝማድ ሳይቀር ይሰደባል:: ይህ ጸያፍና ነውር ነው:: ይህ ክብረ ነክ ነው::

ብዙዎቻችን በነጻነት ሃሳብን ስለመግለጽ ስንሚገት በጣም ኃይለኞች ነን:: ሁሌም መንግሥትን የምንተቸው በዚህ ነው:: እገሌ ብእር ብቻ ነው የያዘው፤ ብእር የያዘን ሰው ማሰር ፍርሀት ነው ምናምን የሚለው ሰው ቁጥር ጥቂት አይደለም:: ነገር ግን የመናገር ነጻነትን በመቀማት ከመንግሥት ይልቅ እኛ እንደምንቀድም ዞር ብለን አስተውለን አናውቅም:: ብናስተውልም እኛ ትክክል እንደሆንን ብቻ ማሰብና ማመንን ባህላችን አድርገነዋል::

ሁሉም ሰው የመናገር ነጻነት መከበር አለበት ብሎ የሚያምነው እሱ ሲናገር ወይም እሱ ሊናገር የፈለገውን ሌላ ሰው ሲናገርለት ነው:: ከዚያ ውጭ የመናገር ነጻነት እሱ መስማት ለማይፈልገውም ሃሳብ እንደሚሰራ አይገነዘብም ወይም ሆን ብሎ ይክዳል:: ይሄ የማህበራዊ ሚዲያ እንቅስቃሴያችን ያጋለጠው ሀቅ ነው::

ዲሞክራሲ በባህሪው ከስር እየተገነባ የሚሄድ እንጂ ከላይ የሚሰጥ አይደለም:: እኛ ግን ከቤታችን ያላሳደግነውን ዴሞክራሲ ነው ከመንግሥት ቢሮ የምንፈልገው:: ቤቱ እየተኮረኮመ ያደገ ሰው ቢሮ ሄዶ በነጻ ሃሳብ የሚያምን ይሆናል ማለት ዘበት ነው:: ህዝብ እርስ በርሱ አንዱ ሌላውን በሃሳብ እየሞገተ ሲያድግ ዴሞክራሲ ያብባል አልያም ግን አንዱ ሌላውን እየጠለፈ እና እያሸማቀቀ የሚቀጥል ከሆነ ዴሞክራሲ እንኳን ሊያብብ እንዲያውም ለአምባገነን መንግሥት መፈጠር በር ሊከፍት ይችላል::

እርግጥ እንደ ህዝብ ካሉብን ችግሮች መካከል እኛ ሊኖረን የሚገባውን ነገር በሙሉ ከመንግሥት መጠበቅ አንዱ ነው:: ለምሳሌ ያህል የትምህርት ጥራት እንዲሻሻል እንፈልጋለን:: ነገር ግን የልጃችንን ደብተር ለማየት፤ የቤት ስራ ለማሰራት ፤ ለማስጠናት ፍላጎት የለንም:: ትምህርት ጥራት ግን የብዙ ነገር ድምር ውጤት ነው:: ካላስጠናን፣ የቤት ስራ ካላሰራን ፣ አጋዥ መጽሐፍትን ካላቀረብን ፤ እንዳይርባቸው ካላደረግን ፣አእምሮአቸው ትምህርት ላይ ብቻ እንዲያተኩር ካላገዝን ፣ ውሏቸውን ካልተከታተልን ልጆች ትምህርት ቤት ውስጥ ብቻ በሚደረግ ስራ ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም:: ያን ሳናደርግ ግን ስለ ትምህርት ጥራት ብናወራ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ የሚለው ተረት በኛ ላይ ይፈጸማል::

ሁላችንም ፍትህ እንዲሰፍን እንፈልጋለን:: ፍርድ ቤት እኛ በምናውቃቸው ሰዎች ላይ የሚወሰነውን እያንዳንዱን ውሳኔ እንከታተላለን ፤ የፖሊስን ችግር እንነቅሳለን ፤ አቃቤ ህግ ብዙ ችግር እንዳለበት እንዘረዝራለን:: እኛ ያለ ጥፋታቸው ታስረዋል ለምንላቸው ሰዎች እንዲህ ስንሚገት ላየን ሰው ስለ ፍትህ ያለን ተቆርቋሪነት በጣም ከፍተኛ ሊመስለው ይችላል::

ነገር ግን በዚያው ልክ ባለስልጣን ዘመድ ካለን ተማምነን ኢ ፍትህዊ ነገር ስናደርግ ቀዳሚዎቹ እኛ ነን:: ለፖሊስ እና ለአቃቤ ህግ ጉቦ ሰጥተን ክስ ስናዘጋም ማንም አይበልጠንም:: ሌላም ሌላም:: እኛ በግላችን ጉዳይ የማናደርገውን ነገር መንግሥት ግን ወንጀል ፈጽመዋል በሚላቸው ሰዎች ላይ እንዲፈጽም እንጠብቃለን::

የብዙዎቻችን ስድቦችም ተቀባይነት የላቸውም:: አንድን ሰው ለሰራው ስራ ቤተሰቡን አብሮ የመውቀስ አዲስ ባህል ሁሉ አምጥተናል:: ልጅን በአባቱ ጥፋት መውቀስ፤ ሚስትን በባሏ ጉዳይ መተቸት፤ እህትን በወንድሟ ጉዳይ ማንጓጠጥን ሃሳብን በነፃነት ከመግለፅ ጋር የምናያይዝ ጥቂት አይደለንም:: ይሄ ኢትዮጵያዊ ባህሪ አይደለም::

ይህ ሃሳብን በነፃነት በመግለፅ ሂሳብ እያዳበርነው ስለመጣነው አምባገነንነት ትልቅ ማሳያ ነው:: ይህ አዲስ ባህል አደገኛ ነው:: አምባገነን ህዝብ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት አይኖረውም:: በፌስቡክ ላይ የሌለውን ዴሞክራሲያው ውይይት በምክር ቤት ልናገኘው አንችልም:: ይህ የሚያመለክተን ነገር ቢኖር እኛ ራሳችን በነጻነት ሃሳብን የመግለጽ መብትን እያፈነን መንግሥት ግን እንዲያከብር እና እንዲያስከብር እንደምንፈልግ ነውና እያስተዋልን::

ስራዬ ብለው ዘርን ሃይማኖትንና ማነትን መሰረት አድርገው ለመሰዳደብና ለመበሻሸቅ ወደ ማህበራዊ ሚዲያው ብቅ የሚሉ ግለሰቦች እዚሁ ሀገር ውስጥ ቢኖሩም በርካቶቹ በውጪ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ናቸው። እርግጥ ነው ማህበራዊ ሚዲያዎችና ተከታዮቻቸውን ተጠቅመው ሀገርና ወገንን የሚጠቅም ለስጋም ለነብስም እረፍት የሚሰጥ አስደማሚ የረድኤት ተግባራትን የሚሰሩ ብዙዎች አሉ።

ከእነሱ በተቃራኒ ስራዬ ብለው ለስድብ የተሰማሩ ግለሰቦች ቁጥር ግን ቀላል አይደለም። በእነዚህ ግለሰቦች ዘንድ የፖለቲካ፣ብሔር ምናምን ጉዳዮች የመሰዳደቢያ አጀንዳዎች መሆናቸው የተለመደ ነው። ይህ ደግሞ እኛ ጋር እንጂ በሌላው ዓለም ስለመኖሩ አጠራጣሪ ነው። ከተማ መኖርና የከተማ ሰው መሆን ይለያያል።

የሰለጠነ ዓለም መኖርና ስልጡን መሆንም እንደዛው። በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የማህበራዊ ሚዲያ ብሽሽቅ የምንታዘበው ነገር ግራ ያጋባል። በየትኛውም ጉዳይ ላይ መሰዳደብ ሃሳብን በነፃነት መግለፅ ተደርጎ እስከመቆጠር፣ እርስበርስ ከፍ ዝቅ ተደራርጎ መዘላለፍ እስከ ድብድብ እስካልደረሰ መብትና የስልጣኔ መገለጫ እየተደረገ ተለምዷል። ከሀገር ርቄያለሁ ብሎ እትብቱ የተቀበረበትን ሀገርም ይሁን ግለሰብ ከጥላቻም የዘለለ የፈለጉትን መናገር ነፃነትን እንደማጣጣም ተቆጥሯል።

ነፃ ንግግር ማለት የጥላቻ ንግግር ማለት እንዳልሆነ በሰለጠነ ዓለም እየኖሩ መዘንጋቱ ይበልጥ አስገራሚ ነው:: ነፃነት ሌሎችን መስደቢያ ወይም ማሸማቀቂያ ፍቃድ አይደለም:: ነፃነት ከባድ ኃላፊነት ነው:: ነፃነት ስድነት አይደለም:: ነፃነት ገደብ የሌለው እንዝላልነትም አይደለም:: ነፃነት ገደቡም ሆነ ኃላፊነቱ ሕሊናዊ ነው:: ነፃነትን ባግባቡ ለመጠቀም እውቀት ይፈልጋል፤ ስነምግባር ግድ ይላል::

በነፃነት ስም ሌሎችን የሚያጥላላና ማንነታቸው ላይ የስድብ ናዳ ማውረድ የነፃነትን እውነተኛ ትርጉም መሳት ነው:: ዘመኑ የዕውቀት ነውና የሃሳብ ልዩነትን በሃሳብ ፍልሚያ ብቻ መታገል የስልጣኔ ምልክት ነው:: እኔ ብቻ ነኝ ልክ፣ እኔ ብቻ አንደኛ፣ እኔ ብቻ ልጠቀም፣ ሌላው የራሱ ጉዳይ የሚል ራስወዳድ አስተሳሰብ ያልበሰለ ሃሳብ ነው::

ብዝሃ ሃሳብን ማክበርና የሌሎችን ማንነት መቀበል የዘመናዊነት ምልክት ነው:: አውሮፓውያን ከጨለማው ዘመን ወደ ሕዳሴው ዘመን የተሸጋገሩት ለብዝሐ ሃሳብ እውቅና በመስጠት ነው:: ከጥላቻ ምንም እንደማይገኝ በመረዳታቸው ነው አሁን ለደረሱበት ሥልጣኔ ብዝሃ ሃሳብን በነፃነት የሚያንሸራሽሩት:: በሃሳብ ተከራክረው፣ ተጨቃጭቀውና ተፋልመው ተቃቅፈውና ተጨባብጠው የሚለያዩት ሰውየው ላይ ሳይሆን ሃሳቡ ላይ በማተኮራቸው ነው::

‹‹ፍቅር የጥላቻ መድኃኒት ነች›› ይባላል:: ሌላውን የሚጠላ ራሱን አይወድም:: ራሱን የሚጠላ እንዴት ሌላውን ሊወድ ይችላል? ፍቅር በማድረጉ፣ ለሌሎች ቅን በማሰቡ፣ ደግ ሥራ በመስራቱ የሚደሰት እንጂ የሚፀፀት ማንም የለም:: ሌሎችን እንደራስ ማየት የሚያረካ እንጂ አያስቆጭም:: ሰው ጥሪው ለፍቅር እንጂ ለጥላቻ አይደለም:: የጥላቻ ንግግር ጠላትን ያበዛል፣ ሰላምን ይነሳል እንጂ ወዳጅን አያተርፍም፤ ፍቅርንም አያመጣም::

ነፃነት ነፃ አይደለም:: የዕውቀትን ዋጋ ያስከፍላል ዕውቀት መዳረሻ አይደለም:: ዕድሜ ልክ የሚደረግ ጉዞ ነው:: አዎ! ነፃነት እውቀት ይፈልጋል:: አለበለዚያ ነፃነት ራሱ ነፃ አይሆንም:: ነፃነት መዳረሻው ሰው መሆን ነው:: ሰው መሆን ደግሞ ከዘረኝነት፣ ከጥላቻ ንግግር አስወጥቶ ከሰብዓዊነት የሚያገናኝ መሠረት ነው:: ሰው ‹‹እውነተኛ ሰው›› ከሆነ ሌላውን እንደራሱ ያያል እንጂ በጥላቻ ንግግር ሰውነቱን አያበላሽም:: ሰው ክቡር ሆኖ ሳለ እንስሶችን መምሰል የለበትም::

ሃሳብ ላይ እንጂ ማንነት ላይ አናተኩር! ነፃነትን ለበጎ ነገር እናውለው:: የጥላቻ ንግግር ለሰዳቢውም ለተሰዳቢውም አይጠቅምም:: ቴክኖሎጂውን ለበጎ ነገር ከተጠቀምንበት ሃሳብን የሚያሳድግ፣ ሕሊናን የሚያበስል፣ ወደፊት የሚያራምድ መልካም ትምህርት ልናገኝበት እንችላለንና::

# ፍረዱኝ

# “መናኸሪያ በሌለበት ከተማ የትራንስፖርት ሪፎርሙን ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ ነው”

**- አቶ ከሊፋ አባ ሳኒ**

**በጅማ ከተማ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ኤጀንሲ ጽሕፈት ቤት የትራንስፖርት አቅርቦት አስተባባሪ**

**ሞገስ ተስፋ፣ ሙሉቀን ታደገ እና መክሊት ወንድወሰን**

ለመንገደኞች ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ከሚያስችሉ የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች መካከል ዘመናዊ መናኸሪያ በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ነው:: አሁን ላይ በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ከተሞች ተመሳሳይ ዲዛይን ያላቸው ዘመናዊ የአውቶቡስ ተርሚናሎች በመገንባት ላይ ናቸው:: ከእነዚህ መካከል የጅማ ከተማ ዘመናዊ አውቶቡስ ተርሚናል አንዱ ነው:: የዛሬው የፍረዱኝ ዓምድ ዝግጅታችን የጅማ ከተማ ዘመናዊ አውቶቡስ ተርሚናል ግንባታ መጓተት ጋር ተያይዞ የተፈጠረ የሕዝብ ቅሬታ ያስመለከትናል::

በ2011 ዓ.ም የተጀመረው የጅማ ከተማ ዘመናዊ አውቶቡስ ተርሚናል ግንባታ ፕሮጀክት በሁለት ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ቀን ቢቆረጥለትም በተባለው ጊዜ መጠናቀቅ አልቻለም:: ለዚህም ፕሮጀክቱን ለመገንባት በወሰደው ተቋራጭ እና ፕሮጀክቱን በሚቆጣጠረው የመንግሥት አካል ድክመት እንደሆነ ቅሬታ ይቀርባል:: የግንባታው መጓተት ለከፍተኛ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተዳርገናል ያሉት የጅማ ከተማ እና ዙሪያ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም አሽከርካሪዎች “የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፍረደን” ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ክፍል አቤት ብለዋል:: የዝግጅት ክፍሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማነጋገር ያገኘውን ምላሽ እንዲህ አሰናድቶታል::

**የአሽከርካሪዎች እና የህብረተሰቡ ቅሬታ**


የጅማ መናኸሪያ በወቅቱ ተገንብቶ አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ ለእንግልት መዳረጋቸውን ለዝግጅት ክፍላችን አቤት ያሉት የአሽከርካሪዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎች በርካታ ናቸው:: የሁሉንም ቅሬታ አቅራቢዎች አቤቱታ በዚህ ዝግጅት ብቻ ማስተናገድ ስለማይቻል እና ሃሳባቸው ተመሳሳይ በመሆኑ የሶስት አሽከርካሪዎችን እና የአንድ መንገደኛ አስተያየት ይዘናል::

በፕሮጀክቱ መዘግየት ችግር ያጋጠማቸው እና ለዝግጅት ክፍላችን ችግራቸውን ከነገሩን አሽከርካሪዎች መካከል ከጅማ አንድ ጊዜያዊ መናኸሪያ ወደ አጋሮ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡት አቶ ሰኢድ ከማል አንዱ ናቸው:: እንደ አቶ ሰኢድ ገለጻ፤ የጅማ ዘመናዊ የአውቶብስ ተርሚናል ግንባታ በተያዘለት ጊዜ ግንባታው ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ባለመሆኑ በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ላይ ጫና እያሳደረ ነው።

አሁን አገልግሎት እየሰጡበት ያለው ጊዜያዊ መናኸሪያ ከተማ አስተዳደሩ “ከጅንአድ” በትብብር ባገኘው ቦታ ላይ ነው:: ቦታው ለመናኸሪያ ታስቦ የተገነባ ባለመሆኑ በየጊዜው ይሰምጣል:: በዚህ የተነሳም በሳምንት ሁለት ጊዜ ድንጋይ እና ጠጠር ይሞላበታል:: ይህ ደግሞ ሀገሪቱ ካላት ሀብት አንጻር ትክክለኛ ርምጃ አይደለም::

ቦታው ረግረጋማ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ተሽከርካሪዎች በጭቃ እየተያዙ እንደሚቸገሩ የሚናገሩት አቶ ሰኢድ፤ በዚህም ለበርካታ ጊዜያት የትራንስፖርት አገልግሎት እንደሚስተጓጐል ያስረዳሉ:: በጊዜያዊ መናኸሪያው ባለው ጭቃ ከተሽከርካሪዎች ባሻገር መንገደኞችም ለመሳፈር እንደሚቸገሩ አመላክተዋል::

እንደ አቶ ሰኢድ ገለጻ፤ በመናኸሪያው ውስጥ ምንም ዓይነት የመንገደኞች ማረፊያና መጸዳጃ ቤት የለም:: ሁሉም ሰው በመናኸሪያው ውስጥ በአገኘው አካባቢ ይጸዳዳል፤ ቆሻሻም ይጥላል:: ይህም ለከፍተኛ የጤና ችግር እየዳረገ ነው:: በተመሳሳይ በዚሁ ቦታ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት የሚቀመጡ መንገደኞች አሉ:: ይህም አሽከርካሪዎችን እና የትራንስፖርት ተጠቃሚዎችን ለከፋ የጤና ችግር እየዳረገ ነው::


ፎቶ- በረሀን ታደሰ

በዘመናዊ አውቶብስ ተርሚናሉ ግንባታ መጓተት ምክንያት ለዝግጅት ክፍላችን ቅሬታ ካቀረቡት አሽከርካሪዎች መካከል ከአጋሮ ጅማ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡት አቶ እንግዳወርቅ አብየ ሌላኛው ናቸው:: እንደ አቶ እንግዳወርቅ ገለጻ፤ ጊዜያዊ መናኸሪያው ጠዋት እና ማታ በጣም ስለሚጨናነቅ መኪና ለማስገባት እና ለማስወጣት ፈተና ነው። ብዙ ጊዜ የተሽከርካሪ ግጭት ይፈጠራል:: በዚህም በተደጋጋሚ የንብረት ውድምት እየደረሰ ነው::

ይገነባል የተባለው የአውቶብስ ተርሚናል በተባለለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ በጊዜያዊ መናኸሪያዎች ራሳቸውን በሕገወጥ የተደራጁ ወጣቶች ተሽከርካሪዎች ለመውጫ ከሚከፍሉት ክፍያ በተጨማሪ ለተራ እንደሚያስከፍሉ ይናገራሉ:: የመናኸሪያ ግንባታ ቢጠናቀቅ አሽከርካሪዎች እና ተሳፋሪዎችን ከሕገወጦች መጠበቅ እንደሚያስችል ያስረዳሉ:: ስለሆነም ከችግሮች ተደራራቢነት አንጻር የተጀመረው የአውቶቡስ መናኸሪያ በአስቸኳይ ሊጠናቀቅ እንደሚገባ ጠቁመዋል::

ሌላኛው አቤቱታ አቅራቢ ደግሞ ከጅማ ወደ በደሌ አገልግሎት የሚሰጠው አቶ ሀኒ ተሰማ ነው:: አቶ ሀኒ ተሰማ በበኩሉ፣ አሁን አገልግሎት እየሰጠ ያለው ጊዜያዊ መናኸሪያ ጭቃ የሚበዛበት እና ረግረጋማ በመሆኑ ለተሽከርካሪ በጣም አስቸጋሪ ነው። ከዚህ ጭቃ ቦታ ለመራቅ ሲሉ አሽከርካሪዎች በሕገ ወጥ መልኩ መንገድ ላይ ይጭናሉ:: በዚህም በተሳፋሪዎች ላይ ከዝርፊያ ጀምሮ በርካታ ችግሮች ይፈጠራሉ:: አሁን ክረምት እየመጣ ነው:: በክረምት ደግሞ በዚህ ጊዜያዊ መናኸሪያ አገልግሎት ለመስጠት የማይታሰብ ነው:: ስለዚህ አስቸኳይ መፍትሔ ሊሰጠው እንደሚገባ አቶ ሀኒ ጠቁመዋል::

ከመናኸሪያው ግንባታ መዘግየት ጋር ተያይዞ ከአሽከርካሪዎች በተጨማሪ የጅማ ከተማ ነዋሪዎች እና ተሳፋሪዎችም ለዝግጅት ክፍላችን አቤቱታ አቅርበዋል:: በአቤቱታ ያቀረቡ የከተማዋ ነዋሪዎች በርካታ ናቸው:: ይሁንና የሰጡን አስተያየት ተመሳሳይ በመሆኑ አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ግለሰብን ቅሬታ ብቻ መርጠን እንደሚከተለው አቅርበናል::

የከተማዋ ተፈጥሯዊ መገኛ ለፖለቲካል ኢኮኖሚ አመች ነው:: በዚህም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ሰዎች ያርፉባታል፤ ይሳፈሩባታልም:: ከዚህ አኳያ የተጀመረው የዘመናዊ አውቶብስ ተርሚናል ፕሮጀክት በከተማዋ እና ዙሪያዋ ለሚደረጉት ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል::

ነገር ግን አሁን ላይ የመናኸሪያው ግንባታ በመጓተቱ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ሰዎች ለተለያዩ ችግሮች ሲጋለጡ ይስተዋላል:: ከተማ አስተዳደሩም ማግኘት የነበረበትን ገቢ እያሳጣው ነው:: በጊዜያዊነት የመናኸሪያ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ቦታዎች የጅማ ከተማን ደረጃ የማይመጥኑ በመሆናቸው የከተማዋን ገጽታ እያበላሹ ነው:: በአጠቃላይ ከመናኸሪያ ጋር ተያይዘው የተፈጠሩ ችግሮች አሳሳቢ በመሆናቸው በአስቸኳይ መፍትሔ እንደሚያሻቸው አመላክተዋል::

**የጅማ ከተማ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ኤጀንሲ ጽሕፈት ቤት ምላሽ**

አቶ ባህሩ ጃድ የጅማ ከተማ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ኤጀንሲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ናቸው:: እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ የከተማው ማህበረሰብ የትራንስፖርት አገልግሎት የተሳለጠ እንዲሆን ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል:: ከዚህ አንጻር በከተማው ውስጥ የሚገኘው የዘመናዊ አውቶብስ ተርሚናል ግንባታ አንዱ ነበር:: ይሁን እንጂ ግንባታውን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት ይሆናል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረው ዘመናዊ የአውቶብስ ተርሚናል በታሰበው ልክ ግንባታው ሊከናወን አልቻለም::

የመናኸሪያ ግንባታ ፕሮጀክቱን ኦማ ኮንስትራክሽን የተሰኘ ተቋራጭ በ2011 ዓ.ም ውል ቢወስድም በተባለው ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ማስረከብ ስላልቻለ ውል እንዲቋረጥ ተደርጓል። አሁን ላይ ዘመናዊ የአውቶብስ ተርሚናል ግንባታ ፕሮጀክቱ “ኦቢኤም” ለተባለ ኮንስትራክሽን ድርጅት የተሰጠ ሲሆን የቁጥጥር ሥራውን የኦሮሚያ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ኤጀንሲ ያከናውናል::

መናኸሪያው ከፍተኛ የሕዝብ ጥያቄ ያለበት በመሆኑና እየተፈጠሩ ካሉ ችግሮች አንጻር በአጭር ጊዜ ገንብቶ ለማጠናቀቅ ርብርብ እየተደረገ ነው። አብዛኛው የፕሮጀክቱ ሥራዎች ተከናውነዋል:: አገልግሎት የሚሰጥበት የሕንፃ ሥራ ተጠናቋል:: አሁን ላይ የሚቀረው ሥራ ውስን ነው:: የቀረው የመናኸሪያው የቤዝ ኮርስ እና የአስፓልት ንጣፍ ሥራ ነው:: ይህን ለማጠናቀቅ የጠጠር እና አስፓልት ንጣፍ ሥራ እየተከናወነ ነው:: ከሁለት ወር በኋላ ተጠናቆ ለትራንስፖርት አገልግሎት ክፍት እንደሚሆን እንጠብቃለን::

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

# “መናኸሪያ በሌለበት ከተማ የትራንስፖርት...

ከገጽ 6 የዞረ



ሌላው በጅማ ከተማ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ኤጀንሲ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ቡድን ጥያቄ የቀረበላቸው የትራንስፖርት አቅርቦት አስተባባሪ የሆኑት አቶ ከሊፋ አባ ሳኒ ናቸው:: አቶ ከሊፋ አባ ሳኒ እንደሚሉት፤ በ2011 ዓ.ም የጅማ ከተማን ዘመናዊ የአውቶቡስ ተርሚናል ግንባታ ፕሮጀክት ውል የወሰደው ኦማ ኮንስትራክሽን ተቋራጭ ነበር:: ይህ ተቋራጭ ከአምስት ዓመት በፊት ሥራውን ሲጀምር ፕሮጀክቱን በሁለት ዓመት ሰርቶ ለማጠናቀቅ ውል ገብቶ ነበር:: ነገር ግን በግንባታ እቃዎች የዋጋ ንረት ሳቢያ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ገንብቶ ሊያስረክብ አልቻለም:: ብዙ መጓተቶችም ተፈጠሩ::

የመናኸሪያ ግንባታው በተባለው ጊዜ ባለመጠናቀቁ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ችግር አጋጥሟል:: አሽከርካሪዎችንና እና ሕዝቡን ለከፋ እንግልት ዳርጓል:: ተሽከርካሪዎቹ ቁመው የሚጭኑበት ምቹ ቦታ አጥተዋል:: ይህን ችግር ለመቅረፍ እንደ ጊዜያዊ መፍትሔ በከተማዋ በሚገኙ መንገዶች (አስፓልት ዳር) የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ሲሞከር ቆይቷል::

ነገር ግን የአስፓልት ዳር አገልግሎቱ ተሳፋሪዎችን እና አሽከርካሪዎችን ለተለያዩ አስከፊ ችግሮች በመዳረጉ ኤጀንሲው ሌሎች አማራጮችን እንዲፈልግ ተገዷል:: በዚህም በጊዜያዊነት ሶስት ቦታዎች ላይ የመናኸሪያ አገልግሎት እንዲጀመር አድርጓል:: እነዚህ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች ሁለቱ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ከወሰዱት ቦታ ትብብር ተጠይቆ የተገኙ ሲሆን አንደኛው ደግሞ ከጅማ ከተማ “ጅንአድ” በትብብር የተገኘ ቦታ ነው:: እነዚህ መናኸሪያዎች ምቹ ባለመሆናቸው አሁንም ሕዝብ እየተሰቃየ ነው:: የተነሳው ቅሬታም ተገቢ እና ትክክል መሆኑን እንደሚረዱ ያምናሉ::

ከፕሮጀክቱ መጓተት ጋር ተያይዞ በተለያዩ ጊዜያት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የተለያዩ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረጋቸውን የሚናገሩት አቶ ከሊፋ፤ ባደረጉት ውይይት ኦማ ኮንስትራክሽን ግንባታውን በተባለለት ጊዜ ማጠናቀቅ ባለመቻሉ የወሰደው ውል እንዲቋረጥ ማድረጋቸውን ይናገራሉ::

ከኦማ ጋር የነበረው ውል በመቋረጡ አሁን ላይ አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ሥራ ለኦቢኤም ኮንስትራክሽን ተሰጥቷል:: አሁናዊ የግንባታ ሁኔታው ጥሩ የሚባል ደረጃ ላይ ነው:: አሁን ላይ ባለው የግንባታ ፍጥነት በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ተናግረዋል::

የኦ.ቢ.ኤም ኮንስትራክሽን ሥራው በምን ያህል ጊዜ እንዲጠናቀቅ ተስማምታችሁ ነበር? ስንል ላነሳንላናቸው ጥያቄ የኦ.ቢ.ኤም ኮንስትራክሽን የፕሮጀክቱን ሥራ የወሰደው በ2015 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ ነው:: ሥራውን በሶስት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ተስማምቶ ነበር:: ነገር ግን እስካሁን ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታው ሳይጠናቀቅ ከስምንት ወራት በላይ መቆጠራቸውን ተናግረዋል::

ቅሬታ አቅራቢዎች ለዝግጅት ክፍሉ ቅሬታቸውን ባሰሙበት ወቅት ላሉት ጊዜያዊ መናኸሪያዎች የመውጫ ይከፍላሉ ነገር ግን በመናኸሪያው ውስጥ በተመሳሳይ ለተራ ተብለው ገንዘብ እንደሚጠየቁ ተናግረዋል:: ለዚህስ የእርስዎ ምላሽ ምንድነው? ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል::

በመናኸሪያ ውስጥም እናንተ ያነሳችኋቸው ችግሮች አሉ:: እነዚህንም ቅሬታዎች ለመፍታት በየዕለቱ የተለያዩ ጥረቶችን እያደረግን ነው:: ለዚህም እንደማሳያ የምናነሳው እንደ ጅማ 31 መስመሮች አሉን:: በ31 መስመሮች የዲጂታል ትኬት ሲስተሞችን ዘርግተን ሥራ እንዲጀምሩ አድርገናል:: በመናኸሪያዎቹ ውስጥም በታሪፍ ተሳፋሪዎችን ያስተናግዳሉ:: ነገር ግን ከመናኸሪያው ውጭ አንዳንድ አገልግሎት ሰጭዎች የዋጋ ጭማሪ ያደርጋሉ::

ይህንንም ለመከላከል ኬላ ላይ ከሚቆጣጠሩ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራን ነው:: ይህ ማለት ግን አንዳንድ ክፍተት የለም ማለት አይቻልም:: የትራንስፖርት ሥራ አስቸጋሪ ነው:: ጠዋት ያለው እና ማታ የሚከሰተው ፈጽሞ የተለየ ነው:: ይሁን እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በየዕለቱ የቁጥጥር እና የክትትል ሥራ መሥራት ያስፈልጋል:: ሚኒኖች ተሳፋሪዎችን ጭኖ ሲወጡ ለከተማዋ ልማት በደረሰኝ የሚደረግ ክፍያ አለ:: አንዳንድ ሕግን የሚተላለፉትን ለማረም ኬላ ላይ ከሚቆጣጠሩ አካላት ጋር በመሆን ሥራዎችን እየሠራን ነው::

የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የሚጠበቅባቸውን የመውጫ ክፍያ ቢፈጽሙም የተደራጁ ወጣቶች ደግሞ የተራ ካልከፈላችሁ መሥራት አትችሉም ብለው ክልከላ ያደርጋሉ:: ይህ አግባብነት ያለው ነገር አይደለም:: ይህንን ለመከላከል ምን እያደረጋችሁ ነው ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄ፤ ሲመልሱ ችግሩ አለ:: ግን ማንም አካል በሰው ንብረት ላይ ተደራጅቶ መሥራት አይችልም:: በተለይ ከጊዜያዊ መናኸሪያዎች ውጭ በመንገድ ላይ ተደራጅተናል የሚሉ ሕገወጦች ‘ሰው አምጥቼለሁ ወይም ሌላ ነገር አድርጌልሃለሁና ገንዘብ አምጣ’ በማለት ከአሽከርካሪዎች ጋር እስጣ ገባ ሲገቡ ይስተዋላል::

ነገር ግን በመናኸሪያ ውስጥ መሥራት የሚችሉት በማህበራት የተደራጁ ወጣቶች ናቸው:: እነሱም የትራንስፖርት አገልግሎቱን የተሳለጠ ማድረግ እንጂ የተራ ማስከፍል አይችሉም:: አልፎ አልፎ ግን ተሳፋሪ ላይ ዋጋ ጨምረው እንዲጫኤን የሚያደርጉ አሉ፤ እነሱንም በተጨባጭ የያዝናቸውን አባረናል:: ከኢ-ትኬት ጋርም እንዲሁ ተቀናጅተው ሕገወጥ ሥራ የሚሠሩ ሰዎችን አባረናል:: በተጨማሪም ከአሠራሩ ውጭ ጅምላ ትኬት ሲሸጡ የተገኙትን ሁለት ሰዎች በአንድ ወር ውስጥ ከሥራ አሰናብተናል:: ህብረተሰቡም ሕጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ አገልግሎት ማግኘት እንዳለበት ግንዛቤ የመፍጠር ሥራም ሰርተናል::

ከተለያዩ ተቋማት ጋር የፕሮጀክት አፈጻጸም ሂደት የልምድ ልውውጣችሁ ምን ይመስላል? ለተባሉትም ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል::

አሁን ላይ በዋናነት ግንባታውን በኃላፊነት እያሠራ ያለው የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ነው:: የሚቆጣጠረውም የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ነው:: እኛ እንደ ቢሮ የምናደርገው ፕሮጀክቱ በተያዘለት ገዜ እንዲያልቅ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ብቻ ነው:: ይህ ሲባል በመናኸሪያ እጥረት ምክንያት እየተፈጠረ ያለውን ችግር በመጥቀስ ግንባታው እንዲፈጥን መጠየቅ ነው የምንችለው:: ከሚመለከተው አካላት ጋር በሃሳብ ደረጃ ውይይት እያደረግን ነው::

በመናኸሪያ አካባቢ የተሽከርካሪ አቅርቦት ችግር የለም:: ከ1100 በላይ የሚሆኑ በተለምዶ አጠራራቸው ኮስትር የሚባሉ ተሽከርካሪዎች አሉ:: 426 የሚሆኑ ታክሲዎች፤ 4400 የሚሆኑ ባጃጆችም እንዲሁ በከተማዋ አገልግሎት ላይ ይገኛሉ:: በባጃጅ ዙሪያ ሕጋዊና ሕጋዊ ያልሆነውን ለመለየት ውይይት በማድረግ ፖሊሲ በማርቀቅና የራሳችን ኮድ በማዘጋጀት ከ11 የባጃጅ ማህበራት ጋር በመሆን ከተለያዩ ቦታዎች በማምጣት ለመንግሥት የሚገባውን ክፍያ ሳይከፍሉና፤ ቦሎ ሳያድሱና መሥራት ካለባቸው አካባቢዎች ውጭ የሚሰሩትን የመለየት ሥራ ተሰርቷል::

በዚህም ሥራ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከ1 ነጥብ 1ሚሊየን ብር በላይ ለመንግሥት ገቢ ማድረግ ተችሏል:: 4400 ባጃጆች ውስጥ ከ3150 የሚሆኑት ብቻ ህጋዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል:: ወደ 37 የሚሆኑ ባጃጆችም ሕገወጥ መሆናቸውን ማጣራት ተችሏል:: ከዚህ በፊት በነበረው አሠራር አንድን ባጃጅ ሶስት እና አራት አሽከርካሪዎች ያሽከረክሩ ነበር:: አሁን ላይ ግን ባዘጋጀነው ባጅ መሠረት አንድን ባጃጅ ያለ ባለቤቱ የሚያሽከረክር ከሆነ ይቀጣል ይህ ወንጀልን ለመከላከል ረድቷል:: መናኸሪያ በሌለበት ከተማ የትራንስፖርት ሪፎርሙን ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ ነው:: ስለሆነም መናኸሪያ አካባቢ ያለውን ችግር መፍታት ለነገ ሊባል እንደማይገባ ጠቁመዋል::

## በኦሮሚያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የኦብኤም ኮንስትራክሽን አክስዮን ድርጅት አማካሪና የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪ ምላሽ

በኦሮሚያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን አማካሪ የጅማ አውቶቡስ ተርሚናል ግንባታ ተቆጣጣሪ ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳኜ አራርሳ እንደገለጹት፣ የአውቶቡስ መናኸሪያውን በ318 ሚሊዮን ብር ለመገንባት በ2011 ዓ.ም ኦማ ኮንስትራክሽን ውል ወስዶ ግንባታ ቢጀምርም በገጠመው የአቅም ማነስ ምክንያት ግንባታው በተያዘለት ጊዜ ሳይከናወን ቀርቷል።

በዚህ የተነሳም ከተቋራጩ ጋር የነበረው ውል ተቋርጦ በ2015 ግንቦት ወር ላይ ግንባታን በ475 ሚሊዮን ብር ለኦቢኤም ኮንስትራክሽን ድርጅት ተሰጥቷል:: ድርጅቱም ግንባታውን በአንድ ዓመት ውስጥ ለማጠናቀቅ ውል ገብቶ ወደ ሥራ ገብቷል::

ኦቢኤም ፕሮጀክቱን ከኦማ ሲረከብ የሲቪል ግንባታ ሥራው 42 በመቶ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር፣ አሁን ላይ የሲቪል ግንባታው ሥራ ከ78 በመቶ በላይ መድረሱን አመልክተዋል። አሁን ላይ የአስፓልት ጠጠር ምንጣፍ (base course) ግብዓት ላይ ችግር እንዳጋጠመ ገልጸዋል።

የአስፓልት ሥራው ለቻይና የኮንስትራክሽን ኩባንያ ለመስጠት ድርድር እየተካሄደ መሆኑን አመልክተው፤ የአስፓልት ንጣፍ ጠጠር (base course) ጥራትን ለማረጋገጥ (ሳምፕል) ለጅማ ዩኒቨርሲቲ መላኩን ጠቁመዋል። ግንባታውን በውሉ መሠረት እስከ ግንቦት ወር ድረስ አጠናቆ ለማስረከብ እየተሠራ መሆኑን፣ አልፎ አልፎ በሚዘንበው ዝናብና በግብዓት አቅርቦት እጥረት ምክንያት በተፈለገው ልክ እየተሠራ እንዳልሆነም ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ጥያቄ ያለበት በመሆኑ የክልሉ መንግሥት በልዩ ትኩረት የሚከታተለው ነው:: ፕሮጀክቱን በተገባው ውል መሠረት ለማጠናቀቅ ጥረት ሲደረግ ነበር:: ነገር ግን የቀረው ጊዜ አንድ ወር ነው:: ዝናብ ካለስቸገረ ምን አልባት አስፓልት ንጣፍ ሥራ ሊሠራ ይችላል:: ነገር ግን አንዳንድ ግብዓት ዕጥረት ሳቢያ ጊዜ ሊወስድ ይችላል:: እንደ እቅዳችን በ2016 በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ ነው::

## የፕሮጀክቱ ሥራ ተቋራጭ / ኮንትራክተር/ ምላሽ

አቶ ለማ ሶራ ይባላሉ የጅማ አውቶቡስ ተርሚናል ግንባታ ሥራ አስኪያጅ ናቸው። ውል ወስዶ ግንባታ ከጀመረ 11ኛ ወሩ ላይ ደርሷል:: ውሉ ለአንድ ዓመት የተወሰደ ነው:: ከዚህ በፊት ከነበረው ኮንትራክተር ውል ስንወስድ በርካታ ችግሮች የነበሩበት በመሆኑ ብዙ ጊዜ ወስዷል:: አሁን ላይ የሕንፃውን የአሉሚኒየምና የቀለም ሥራ ተሠርቷል::

የተርሚናሉ ሥራ ከአካባቢው የአየር ጸባይ ጋር ተዳምሮ ፈታኝ ነው። የሆነ ቦታ ሥራ ሲሰራ ውሃ ይመነጫል፤ ይህን እንደገና ለማድረቅ ጊዜ ይወስዳል:: አሁን ላይ ከፊል መሠረቱ ተጠናቋል:: የቀረው ትልቁ ሥራ ቤዝ ኮርስና አስፓልት ንጣፍ ነው:: ፕሮጀክቱ ከፍተኛ የሕዝብ ጥያቄ ያለበት በመሆኑ ችግሩን የሚመጥን ምላሽ ለመስጠት ርብርብ እየተደረገ ነው::

ውል የተወሰደው ለአንድ ዓመት ነው:: አሁን ላይ 11ኛ ወር ላይ ነን :: ስለዚህ በዚህ አንድ ወር ይህን ግንባታ ማጠናቀቅ ትችላላችሁ ተብለው የተጠየቁት አቶ ለማ በምላሻቸው፤ ቀድሞ ከነበረው ውል ተቋርጦ በአዲስ መልክ ውል ተይዞ ወደ ግንባታ ሲገባ ብዙ ፈተናዎች ነበሩ:: ለማስተካከል ብዙ ጊዜ ወስዷል:: አሁን ላይ የቀረው የጠጠርና የአስፓልት ንጣፍ ሥራ ነው::

ሕዝቡ የሚያነሳውን ችግር እንረዳለን:: እንደ ክልልም ችግሩን ለመፍታት ርብርብ እየተደረገ ነው:: የቤዝ ኮርስ ዋጋ ከውሉ በላይ ገንዘብ የሚጠይቅ ሆኗል:: ይህን አቻችሎ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው:: የቀረው የውል ጊዜ አንድ ወር በመሆኑ ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው::

## የጋዜጠኞች ትዝብት

ፕሮጀክቱ ለሌላ ተቋራጭ ቢሰጥም አሁንም ከግብዓት እና መሰል ችግሮች ጋር ተያይዞ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ሊጠናቀቅ እንደማይችል ታዝበናል:: የአስፓልት ንጣፍ ሥራውንና የቤዝ ኮርስ ሥራው ገና አልተጀመረም:: አስፓልቱን ለማሠራት ከቻይና ድርጅት ጋር ድርድር አልተጀመረም:: ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ዘመናዊ የአውቶብስ ተርሚናሉ ግንባታ በቀሪው አንድ ወር ሊጠናቀቅ የሚችል አይደለም፣ አስፈላጊው ርብርብ ካልተደረገ መጪው የክረምት ወር ከመሆኑ አንጻር በዚህ ዓመት ስለመጠናቀቁ ርግጠኛ መሆን አይቻልም::

እንደ አማራጭ ተወስደው በጊዜያዊነት እያገለገሉ ያሉ መናኸሪያዎች ማረፊያና መጸዳጃ ቤቶች ባለመኖራቸው ለአሽከርካሪዎችም ሆነ ለመንገደኞች ጤንነት አደጋ ደቅነዋል::

# ነፃ ሃሳብ

## ቁርሾዎችን የሚያክመው፤ የፖለቲካ ባሕልን የሚያርቀው ምክክር

**ታሪኩ ዘለቀ**

ዓለም በርካታ የፖለቲካ ስሪትን ያለፈች፣ እያለፈች ያለችም፣ ወደፊትም የምታልፍ ነች:: አንድ የነበሩ ሀገራት ብዙ ሆነው፣ብዙ የነበሩ አንድ ሆነው አይተናል፣ ሰምተናል፣ እየሆነም ነው:: ኢትዮጵያም በእነዚህ ውስጥ በአንዱ ወይም በሌላው አልፋለች::

ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያላት ሀገር ብትሆንም የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት ሳይኖራት ብዙ ክፍለ ዘመናትን ተሻግራለች:: ሁሉም በሚባል ደረጃ መንግሥታቷ ስልጣን የሚያስረክቡት በኃይል ሲሆን ይህም ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል::

ሀገራችን ኢትዮጵያ ረጅም ዘመናት የቆየችበት ጤናማ ያልነበረው የፖለቲካ ሂደቷ በርካታ ውስብስብ ችግሮችን እንድታስተናግድም አድርጓታል:: በየጊዜው የሚመጡት መንግሥታትም ልዩነቶችን በውይይትና በድርድር ከመፍታት ይልቅ አፈሙዝን ቀዳሚ ምርጫቸው በማድረግ አመጾችን፣ ሕዝባዊ ንቅናቄዎችን እና የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎችን ሲያስተናግዱ መኖራቸው የሚታወስ ነው::

የመንግሥታቱ ያላዛለቀውና የማያዛልቀው ምርጫዎቻቸውም እንደሀገር መሠረታዊ ቅራኔዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆነዋል:: በእነዚህ ጥቅል የዘመናት ችግሮችም በየጊዜው የሰው ሕይወት ጠፍቷል፤ በርካታ ሀብት ንብረት ወድሟል:: በሕዝቦች መካከልም መቃቃርና መጠራጠር ተፈጥሮ እንደሀገር አሁን የደረስንበት የጎጥና የጥላቻ ፖለቲካ ላይ አርፈናል::

ይህም በመሆኑ የፖለቲካ ባሕላችንን ማዘመንና የተሄደበትን መንገድ መቀየር የዚህ ትውልድ የቤት ሥራ ሆኗል:: ለኢትዮጵያ ፈተና የሆነባትን ችግር ከሥር መሠረቱ ማወቅና መረዳት መፍትሔም ማፈላለግ ተገቢ ነው:: አሁን ላይ በልዩነት መነፅር ውስጥ የምትዋልል ሀገር ለነገው ትውልድ አስቀምጦን ማለፍ ለታሪክ ተወቃሽነት ለህሊናም ፀፀት የሚዳርግ ነው::

ነገን ዛሬ እንስራ የሚል እሳቤና ፍልስፍና በዓለም ላይ በናኘበት በዚህ ዘመን እኛ ትላንት ላይ ቆመን መቆዘም ረብ የለውም:: ለዚህም ከፋፋይ ትርክቶችን እየዘጋን ወደ አሰባሳቢ ትርክቶች የሚወስዱ መንገዶችንና አሠራሮችን ብሎም የርዕዮተ ዓለም እሳቤዎችን ገቢራዊ ማድረግ ሀገርን መታደግ ነው::

ለዚህም ነው የዘመናት ጥርቅም ችግሮቻችንን ለመፍታት፣ ሰላም የሰፈነባትና ለቀጣዩ ትውልድ የተሻለች ሀገር ለማስረከብ ያስችላል በሚል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ በርካታ ተግባራትን እየከወነ የሚገኘው:: ትልቅ ኃላፊነት የተጣለበት ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለሀገራችን ብሩህ ተስፋን ይዞ እንደመጣ በብዙዎች ታምኖበታል::

ምክንያቱም መመካከር ፀብን የሚያርቅ፣ ሕዝብን የሚያቀራርብ፣ መፍትሔ የሚያመነጭ መድረክ በመሆኑ ነው:: እንደ ሀገር በመሠረታዊ ቅራኔዎች ተወጥረን በምንገኝበት፣ አለመስማማቶች ሰፍተው በሚታዩበት፣ በተለይ ከፖለቲካ በሚመነጩ መሠረታዊ ቅራኔዎች በምንታመስበት በአሁኑ ወቅት ውይይት ተገቢው መንገድ ነው:: አሉ የሚባሉ ቅራኔዎችን ለመፍታትም ያልተሞከረውና እንደ ትልቅ ተስፋ የሚታየው ቁጭ ብሎ መመካከር ነው::

የሀገራዊ ምክክር አስፈላጊም ጠቃሚም ነው:: አለመግባባት የፈጠሩትን ጉዳዮች ወደ መድረክ አምጥቶ ሕዝቡ እንዲወያይበት ያደርጋል:: እንደ ሀገር በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተመሳሳይ አመለካከት ለማዳበርና ሀገሪቱን ወደ ሰላም እንድትመጣ፣ ወደ እድገት እንድትጓዝ ለማድረግ ታስቦ የተቋቋመ የምክክር መድረክ ነው:: አላማው የተቀደሰ ነው::

ሀገራዊ ምክክሩ ያስፈለገው በሀገራዊ ጥቅምና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነቶችና አለመግባባቶች መኖራቸው ነው:: ሥራው ለኮሚሽኑ ብቻ የሚተው አይደለም:: የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምክክር ኮሚሽኑ እቅድ መሳካት መትጋትና ከልዩነቶች ይልቅ የሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የነገዋን ኢትዮጵያ አስበው መሥራት ይኖርባቸዋል::

> **ነጣይ ትርክቶችን በመቅረፍ የጋራ እና አንድ ወደሚያደርጉ ትርክቶች ለመምጣት የተለያዩ ውይይቶች ያስፈልጋሉ**

ሂደቱ ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ከፍ ያለ ነው:: ፖለቲካ ፓርቲዎች ሀገራዊ ምክክሩ ቢያንስ ያሉብንን መሠረታዊ ቅሬታዎች ለመፍታት የሚያመላክት መድረክ መሆኑን ማመንና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: የምክክሩን ሂደት በንቃት የሚሳተፍ እና ሃሳብ የሚያቀርብ፣ መፍትሔዎችን የሚጠቁም አካል/ቡድን በመደበኛነት መድበው መንቀሳቀስ አለባቸው::

ፓርቲዎች የሚታገሉለት አላማ፣ የሚከተሉት ርዕዮተ ዓለም ሊሳካ የሚችለው ሀገር ሲኖር ብቻ ነው:: ያለችን ሀገር አንድ እስከሆነች ድረስ ለሀገራችን ችግሮች መፍትሔ በሚያመነጭ ምክክር ላይ ከሁሉም በላቀ የፓርቲዎች አስተዋፅኦ የገዘፈ ነው:: ፓርቲዎች ሰላም ከሌለና አሁን በሚታዩ አዝማሚያዎች የሚቀጥሉ ከሆነ ወጥቶ መግባት ሰርቶ መብላት አለመኖሩን ከሌላው አካል በበለጠ ስለሚገነዘቡ ምክክሩ እንዲሳካ የየእለት ተግባራቸው መሆን አለበት::

የፖለቲካ ፓርቲዎች የምክክር ኮሚሽኑ አላማ እንዲሳካ ርብርብ ማድረግ የውዴታ ግዴታቸው ነው:: ለምክክሩ ልዩ ትኩረትም ሊሰጡት ይገባል:: ጉዳዩን ሰፋ አድርገው በመመልከት ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል:: ሃሳቦችን አሰባስበው ወደ ኮሚሽኑ ማስተጋባት አለባቸው:: የምክክሩ ውጤት ወደ ተግባር እንዲለወጥና ሕዝቡ ሰላማዊ በሆነ መንፈስ ተወያይቶ፤ ልዩነቶችን በሰላም እየፈታ ሀገሩን እንዲያሳድግ የፓርቲዎቹ ሚና የላቀ ነው::

የምክክር ውጤቱ ውጤታማ እንዲሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች ልዩነታቸውን በመተው የነገዋን ሀገር አስበው ከምክክር ኮሚሽኑ ጋር በጋራና በትብብር መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: ብሔራዊ ምክክሩ በተሳካ ሁኔታ እንዲከናወን የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዜጋ በንቃት ሊሳተፍ ይገባል::

በተለይ ደግሞ ወጣቱ ትውልድ አደባባይ የሞሉ ትርክቶችን ከራሱ፣ ከማህበረሰቡ፣ ከሀገር ተጠቃሚነት አንፃር በሰከነ መንፈስ ሊመረምራቸው ይገባል:: ለምን ብሎ የሚጠይቅና ሁኔታዎችን በጥልቀት የሚመለከት መሆን አለበት::

አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል የሚሸፍነው ወጣቱ ትውልድ ለብሔራዊ መግባባት መሠረት የሚጥሉና የነጠሩ ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ በመተንተን፣ በማስገንዘብና ለሀገራዊ አንድነት አብዛኛውን ዜጋ ሊያስማሙ፣ ሊያቀራርቡ የሚችሉ አማራጮችን ማቅረብ መገለጫው ሊሆን ይገባል::

ወጣቱ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ዜጎች ሀገራችን እየተፈታተናት ከሚገኘው አደገኛ ትርክት ወጥታ ወደ አሰባሳቢ ትርክት ልትመጣ የምትችልበትን መላ ማዋጣት፣ ለገቢራዊነቱም መሥራት ይጠበቅብናል::

ኢትዮጵያ በታሪክ ቅብብሎሽ የብዙ አኩሪ ታሪክ ባለቤት ብትሆንም በዘመናት ቆይታ ውስጥ ግን በፖለቲካው እንዲሁም በማህበራዊ ጉዳዮች በተፈጠሩ ነጣጣይ ትርክቶች ዛሬ ላይ የግጭት መነሻ ምክንያት እየሆኑ መጥተዋል:: ይህን አሳሳቢ ችግር ለመቅረፍም አሰባሳቢ ትርክቶች ወይም የጋራ ተግባቦት የሚፈጥሩ ትርክቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ያስፈልጋል::

ብዙዎች እንደሚሉት ሀገራችን ላይ የሚታዩ የትርክት ዓይነቶች ሁለት ዓይነት ይዘት አሏቸው:: አንደኛው አቅላይ ትርክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የወል ወይም ገዢ /አሰባሳቢ ትርክት ነው:: የመጀመሪያው የትርክት ዓይነት ነጠላ ጉዳይ ላይ ትኩረት በማድረግ ራስን ብቻ የሚመለከት ‹እኔ ብቻ› የሚል ስሜትን የያዘ ነው:: ሁለተኛው የትርክት ዓይነት ደግሞ ብዝሀነትንና አካታችነትን የሚይዝ ነው::

በርግጥ ኢትዮጵያ ብዝሀነትንና አካታችነትን የሚያንፀባርቁ በርካታ አሰባሳቢ ትርክቶች አሏት:: እነዚህን ትርክቶች እንዴት እንጠቀምባቸው? እንዴት ሊያሻግሩን ይችላሉ? በሚሉ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ውይይትና ምክክር ማድረግ ያስፈልጋል:: በተቃራኒው ታሪክን ማዛባት ልማድ የሆነበትን አላስፈላጊ ፖለቲካ ማፅዳት ተገቢ ነው:: በእውነትና በልክ ማስቀመጥ ግዴታ ነው:: ትርክቶችን በአግባቡ ማስተናገድ እንደሚገባ ሁሉ ከጀርባቸው የያዙትን መልእክትና ዓላማም አብጠርጥሮ ማወቅ ግድ ይላል::

አሁን አሁን ከግለሰብ ወይም ከቡድን የሚመነጩ ነጣጣይ ትርክቶች ሀገር ላይ ተፅእኖ እያሳደሩ ይገኛሉ:: ግጭቶች ይከሰታሉ:: እነዚህ ግጭቶች በአብዛኛው መነሻቸው የግለሰቦች፣ የቡድኖች ፍላጎት ሊሆን ይችላል:: ከተወሰኑ ቡድኖች አካባቢ ሊነሱ ይችላሉ:: የራሳቸውን ጥቅም፣ የራሳቸውን ፍላጎት፣ ራሳቸው ሊያሳኩ የፈለጉትን ግብ በትርክት መልክ ይዘው ሊመጡ ይችላሉ::

እነዚህ ትርክቶች የሌሎች ወገኖችን ፍላጎት የሚነኩ ይሆኑና በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ወደ ግጭት ያመራሉ:: ግጭቶች እያደጉ ሲሄዱ ደግሞ ተፅዕኗቸው ወደ ሀገር ይመጣል:: ሀገርን ወደ መበጥበጥ፣ ሀገርን ወደ መበተን፣ በጋራ አለመቆምን፣ በጋራ አለመሥራትንና አለመሰባሰብን ያስከትላል::

እንዲህ ሲሆን አንድ መሆናችን፣ በጋራ መቆማችን የሚያንገበግባቸው የኢትዮጵያ ጠላቶች ደግሞ ዓለም የደረሰችበት የእድገት ደረጃ ያመጣው የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ሀገርን በሚያፈርስ መልኩ ጨምረውበት ያስተጋቡታል:: ይህም አሰባሳቢ ትርክት ለመፍጠር አንዱ ጋሬጣ ነው::

በማህበራዊ ትስስር ገፆች የሚወጡ መረጃዎች እንዲሁም በአንዳንድ መደበኛ መገናኛ ብዙሃን የሚለቀቁ መረጃዎች አሰባሳቢ ትርክትን ለመፍጠር ተግዳሮት እየሆኑ መጥተዋል:: ማህበራዊ ሚዲያዎች መደበኛ ባልሆነ መንገድ /ኢንፎርማል የሚቋቋሙ፣ ተቋማዊ ይዘት የሌላቸው በመሆናቸው እነሱ በሚፈጥሯቸው የተዛቡ መረጃዎች ምክንያት ማህበረሰቡ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ የሚሄድበት አጋጣሚ ሰፊ ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ መደበኛ መገናኛ ብዙሃኑ መደበኛ የሆነ አካሄድን ጠብቆ ተቋማዊ አሠራርን ተከትሎ የሚሄድ ነው:: የራሱ የሆነ ሥርዓትና ደንብ አለው:: መረጃ ለህብረተሰብ ሊሰጥ ሲፈለግ አሁን ያለው የማህበረሰብ ክፍል ትኩስና የሚያጋግል መረጃዎችን፣ ስሜት ኮርኳሪ ጉዳዮችን ይፈልጋል:: ይህንን እንዳያደርግ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለበት:: ሕግን አክብሮ በመንቀሳቀሱም በማህበራዊ ሚዲያ የመበለጥ ተግዳሮት ገጥሞታል::

ይህም መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ከሆነ ሰነባብቷል:: በመሆኑም ለግጭት መንስኤ የሆኑ ትርክቶችን በሚያመነጩና በሚያሰራጩ አካላት ላይ ተጠያቂ የሚያደርግ ሥርዓት ሊበጅ ይገባል:: አንዳችን በአንዳችን ላይ ጦር የሚያማዝዙ አማዘውም ያየናቸው በርካታ ትርክቶችን ይዘው አደባባይ ሲወጡ እየተመለከትን ነው:: ይሄንን የሚቆጣጠር አካል የለም ወይ ያስብላል:: ጥላቻን ለሚሰብክ ሀሰትን ለሚነዛው ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ ያስፈልጋል::

ነጣይ ትርክቶችን በመቅረፍ የጋራ እና አንድ ወደሚያደርጉ ትርክቶች ለመምጣት የተለያዩ ውይይቶች ያስፈልጋሉ:: ለዚህም ብሔራዊ ምክክሩ ወሳኝና አስፈላጊ ነው:: የሕዝብ ውይይቶች ወደ ጋራ አንድነት ያመጣሉ:: ተነጋግሮ ተደማምጦ ችግሮችን ፈትቶ ለመሰባሰብ አንድ ለመሆን ይበጃሉ::

አሰባሳቢ ትርክቶችን ከታች ጀምሮ በኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በማካተትና እንዲጎለብቱ በማድረግ ትውልድ የሚማርበትን አካሄድ መዘርጋት ያስፈልጋል:: በሁሉም በሚቀርቡ የትምህርት ዓይነቶች አሰባሳቢ ትርክቶችን በማስገባት ቢሰራባቸው ጥሩ ዜጋ ማፍራት ይቻላል::

የጋራ ገዢ ትርክቶች በጋራ ለመፍጠር የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ከፍ ያለ ቢሆንም መገናኛ ብዙሃን፣ የሚታተሙ የሕትመት ሥራዎች እንዲሁም የኪነጥበብ ባለሙያዎች ሀገራዊ ኃላፊነት ትልቅ ነው::

በአጠቃላይ ነባር ሀገራዊ ችግሮቻችንን በሀገራዊ ምክክር እና በሽግግር ፍትህ ማረም ይገባናል:: የገጠሙን የግጭትና የጦርነት ፈተናዎችን ለመሻገር ደግሞ ሰላማዊ የፖለቲካ አካሄዶችን ተመራጭ ማድረግ አለብን:: በኢትዮጵያ ታሪክ በርካታ የእርስ በእርስ ግጭቶች እና ጦርነቶች ተከስተው እንደ ሀገር ከባድ ኪሳራ ደርሶብናል:: የዚህም ምክንያት ግጭቶችን በውይይትና በስምምነት የመፍታት የፖለቲካ ልምምድ ስለሌለን ነው::

በመሆኑም ፖለቲካችንን ከግንባር ወደ ጠረጴዛ፣ ከጫካ ወደ አዳራሽ እንዲመለስ ማድረግ የሁላችንም የዜግነት ግዴታችን ነው:: ከበዳይ ተበዳይ አዙሪት ልንወጣ ያስፈልጋል። በምሕረት፣ በይቅርታ፣ በካሣና፣ በፍትሕ ታክመን ወደፊት መጓዝ መቻል አለብን። ለዚህ ስኬትም ኢትዮጵያውያን ሁሉ በንቃትና በብቃት ልንሳተፍ ይገባናል። መንግሥትም የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አተገባበርን ከሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ጋር የተናበበ እና የሚመጋገብ እንዲሆን በማድረግ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት!

# ሀብት የማሰባሰቡን ሥራ እቅድ በላይ የፈፀመው ካፒታል ገበያ

ፍሬሕይወት አወቀ




የኢትዮጵያ የሰነድ መዋዕለ ነዋዮች /ካፒታል/ ገበያ በካፒታል ገበያ አዋጅ መሠረት በኢትዮጵያ መንግሥትና በግሉ ዘርፍ አጋርነት የተቋቋመ የመጀመሪያው ኩባንያ ነው። የገበያው ዋና ዓላማ የኢኮኖሚ ዕድገትን ማሳለጥ፣ የፋይናንስ አካታችነትን ማበረታታት እና ለኢትዮጵያውያን ጥሪት (ሀብት) መፍጠር ነው።

ገበያው ድርጅቶች ካፒታል የሚሰበስቡበትን መድረክ በመፍጠር የኢንቨስትመንት ዕድል በማመቻቸት እንዲሁም የድርጅቶች መልካም አስተዳደርና ግልጽነትን በማበረታታት ገበያው በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ የለውጥ ጉዞ ላይ ጉልህ ሚና እንዲጫወት ማድረግንም ያለመ ነው።

ገበያው የተቋቋመው በወርሃ ጥቅምት 2016 ዓ.ም ሲሆን፣ መንግሥት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በኩል የ25 በመቶ የተፈቀደ ካፒታል ድርሻ ሲይዝ፣ የግል ዘርፉ ደግሞ ቀሪውን 75 በመቶ ድርሻ የያዘ ነው። በዚህም መሠረት ካፒታል የማሰባሰብ ሥራው ተከናውኗል።

በካፒታል የማሰባሰብ ሂደት የታየው ከፍተኛ ተነሳሽነትና ፍላጎት እንዲሁም ርብርብ ኢትዮጵያ እያካሄደች ላለችው የፋይናንስ ዘርፍ ልማትና ኢኮኖሚ የገበያው ተግባራዊ መሆን ዓይነተኛ ድርሻ እንዳለው የዘርፉ ባለሙያዎችም ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ሰነድ መዋዕለ ነዋዮች ገበያ በቅርቡ ለጋዜጠኞች በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ለገበያው የሚያስፈልገውን ሀብት የማሰባሰብ ሥራ ሂደት በስኬት መጠናቀቁን አስታውቋል። በመግለጫው ላይ እንደተመለከተው፤ ገበያው ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆንም፣ የሀብት ማሰባሰብ ሥራውን ከታቀደው በላይ ማሳካት ተችሏል፤ ይህን ካፒታል የመሰብሰብ ሥራም በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ተችሏል። በዚህም በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሀብቶች ተሳትፈዋል።

የኢትዮጵያ ሰነድ መዋዕለ ነዋዮች ገበያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ጥላሁን እስማኤል እንዳሉት፤ ገበያው በካፒታል ገበያ ሥርዓት ውስጥ ማዕከላዊ የሚባል ዋና ሚና ይጫወታል፤ በመንግሥት በኩል ገበያውን የማቋቋም ኃላፊነት የወሰደው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሲሆን፣ እሱም የ25 በመቶ ካፒታል ድርሻውን ጨምሮ ገበያውን የማቋቋም ኃላፊነቱን ተወጥቷል።

የኢትዮጵያ ሰነድ መዋዕለ ነዋዮች ገበያ በበኩሉ ቀሪውን 75 በመቶ ካፒታል ከግሉ ዘርፍ የማሰባሰብ ኃላፊነቱን በመወጣት የሀብት ማሰባሰብ ሥራውን በስኬት ማጠናቀቅ ችሏል ሲሉ ዶክተር ጥላሁን አስታውቀዋል። ለዚህም የውጭ የኢንቨስትመንት አማካሪዎችን በመቅጠር ጭምር መሥራቱን ጠቅሰው፤ የአዋጭነት ጥናት፣ የቢዝነስ ፕላንና ሌሎች የቴክኖሎጂ ፍላጎቶችና ኩባንያውን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ የካፒታል፣ የቴክኖሎጂ፣ የሰው ኃይልና የሕግ ሥርዓቶችን የመሥራት ተግባሮች መከናወናቸውን ተናግረዋል።

ኩባንያው በተቋቋመ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የኩባንያው ቦርድ በፍጥነት እየተገናኘ የካፒታል ማሰባሰብ ሥራውን ሲሰራ እንደቆየ አመልክተው፣ በዚህም በአጠቃላይ የተገኘው ውጤት አስደሳች እንደሆነና ለመሰብሰብ ከታቀደው ካፒታል 631 ሚሊዮን ብር (11.07 ሚሊዮን ዶላር) በላይ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር (26.6 ሚሊዮን ዶላር) ካፒታል ማሰባሰብ መቻሉን ተናግረዋል። ይህም የዕቅዱን ከ220 በመቶ በላይ የሚበልጥ ሲሆን፤ በዚህም 48 በፋይናንስና ከፋይናንስ ውጭ ባሉ ዘርፎች የተሰማሩ ተቋማዊ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች መሳተፋቸውንም አስታውቀዋል።

ዶክተር ጥላሁን እንዳብራሩት፤ ከእነዚህም መካከል በዋናነት 16 የሀገር ውስጥ ባንኮች፣ 12 ኢንሹራንስ ኩባንያዎች እና ሌሎች 17 ከፋይናንስ ተቋም ውጭ ያሉና በአምራች ኢንዱስትሪዎች የተሰማሩ ተቋማት ተሳትፈዋል። ከውጭ ባለሀብቶች መካከልም የናይጄሪያ ትሬድ ኤንድ ዴቨሎፕመንት ባንክ ግሩፕ እና ሌሎች ኩባንያዎችን ጨምሮ በጋራ 250 ሚሊዮን ብር በሚደርስ ገንዘብ ተሳታፊ የሆኑ ድርጅቶች ናቸው።

ይህም ትልቅ ውጤት እንደሆነ የገለጹት ዶክተር ጥላሁን፤ በተለይም ከሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በዋናነት ከተሰራው የሀብት ማሰባሰብ ሥራ በላይ አጋርነትን ለመፍጠር የተሄደበት ረጅም ርቀት ውጤታማ እንደነበር ጠቅሰዋል። በዚህም ከተቋማቱ ጋር በተደረጉ የተለያዩ ውይይቶች የመዋዕለ ነዋዮች ገበያን ምንነት እንዲረዱ ዕድል መስጠቱን ተናግረው፣ ኢንቨስትመንቱም ከ10 ሚሊዮን እስከ 150 ሚሊዮን ብር መሆኑን ገልጸዋል።

**ለመሰብሰብ ከታቀደው ካፒታል 631 ሚሊዮን ብር (11.07 ሚሊዮን ዶላር) በላይ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር (26.6 ሚሊዮን ዶላር) ካፒታል ማሰባሰብ ተችሏል**

እነዚህ ባለሀብቶች የሰነድ መዋዕለ ነዋዮች ገበያ ባለቤት መሆናቸው ብቻ ሳይሆን አገልግሎት አቅራቢ እንዲሆኑ ፍላጎት አለ ሲሉ የጠቀሱት ዶክተር ጥላሁን፤ አሁንም ቢሆን የመዋዕለ ነዋይ ሰነዳቸው በካፒታል ገበያ ላይ ሙሉ ለሙሉ መተማመን እንዳላቸውና ለሌሎች አገልግሎቶችም ዝግጁ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው ብለዋል። ገበያው በተለይም አገናኝ አባላት የሆኑ ብሮከሮች እንደሚያስፈልጉት አመልክተው፣ አገናኝ ሆነው የመምጣት ዕድሎች እንዳላቸውም አስረድተዋል።

‹‹የካፒታል ገበያ ሥርዓት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትልቅ ተስፋ ያለውና ብዙ ሥራ ሊሰራበት የሚገባ ነው›› ያሉት ዶክተር ጥላሁን፤ አብዛኞቹ ባለሀብቶችም ይህንኑ በመረዳት የአጭር ጊዜ ትርፍን ሳይመለከቱ ስትራቴጂክ የሆነ ድጋፍ ለማድረግ ኢንቨስት ማድረጋቸውን አስታውቀዋል። ስትራቴጂክ ድጋፍ ወይም ስትራቴጂክ ኢንቨስተር ማለት ደግሞ በአጭር ጊዜ ከሚገኝ የግል ጥቅም በላይ ሀገራዊ ጥቅምን ያስቀደመ ማለት እንደሆነ አብራርተው፣ ለዚህም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከፍተኛ ርብርብ ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኩባንያዎች ከፍ ያለ የካፒታል ፍላጎት ባሳዩ ጊዜ በገበያ ሥርዓት ውስጥ ገብተው መገበያየት ይችላሉ። ይህም ለእያንዳንዱ ኩባንያ እሴት እንዲጨምር ያስችለዋል። ከዚህም ባለፈ የፋይናንስ ተቋማት ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋትና ለማሻሻል እንዲሁም ለአዳዲስ ጀማሪ የፋይናንስ ተቋማት ጭምር በር ይከፍታል፤ የፋይናንስ ተቋም ላልሆኑ ድርጅቶችም እንዲሁ ካፒታል ገበያ የረዥም ጊዜ የፋይናንስ ማግኛ አማራጭ ሆኖ ያገለግላል።

‹‹በአብዛኛው የአክሲዮን ገበያ ሽያጭም ሆነ የሰነድ መዋዕለ ነዋይ ዋጋን የሚወስነው ገበያው ቢሆንም ኩባንያው ቁጥጥር ያደርጋል›› ያሉት ዶክተር ጥላሁን፤ ቁጥጥር የሚያደርገውም በሁለት ዓይነት መንገድ መሆኑን ገልጸዋል። አንደኛው ሁልጊዜ ገበያው ሲጀመር ከዚህ ዋጋ በላይ እንዳይጨምር እንዳይቀንስ በማለት ወስኖ ሊጀምር ይችላል ሲሉ ጠቅሰው፣ ይህም ተገበያዮች በምን ያህል የዋጋ መጠን እንደሚገበያዩ አውቀው እንዲጀምሩ ዕድል እንደሚሰጣቸው ተናግረዋል።

ሌላው ከሚሸጡ አክሲዮኖች ጋር የተገናኘ ልዩ የሆነ የዋጋ ገደብ ሊወጣላቸው እንደሚችልም ጠቅሰው። ይህም ብዙ ጊዜ በታዳጊ ሀገራት የተለመደ ነው ብለዋል። ገበያው ሲጀምር የኢትዮጵያ የሰነድ መዋዕለ ነዋዮች ገበያ ዋጋን በመቆጣጠር ደህንነቱ የተጠበቀ የገበያ ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ ዋነኛ ሥራው እንደሆነ ገልጸዋል።

የአክሲዮን ሰነድ መዋዕለ ነዋዮች ሽያጭን በተመለከተ በቀጣይ የቴክኖሎጂ፣ የልምድ ልውውጥ ማድረግና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት ይጠይቃል ያሉት ዶክተር ጥላሁን፤ በተለይም ገበያው ላይ መጥተው ለሚሳተፉ ኩባንያዎች ስለ ገበያው ሥርዓት ማስተማርና ግንዛቤ መፍጠርን፤ ባለሀብቶችንም እንዲሁ ማስተማርን ይጠይቃል ብለዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት ግንዛቤ መስጠቱ ወይም ትምህርቱ በዋናነት ቁጠባን ለማስለመድ ሲሆን፤ ለአብነትም ዛሬ ላይ በትንሹ ከ5000 እስከ 15000 ብር ካወጣ፣ በቀጣይ ይህ ገንዘብ ቢያንስ አንድ አክሲዮን ሊያስገዛ እንደሚችል በማስረዳት በተለይም የረጅም ጊዜ የቁጠባ መንገድ የለንም የሚሉ ወጣቶች ከአምስትና አስር ሺ ብር ጀምረው እንደ ኢትዮ ቴሌኮም ከመሳሰሉ ተቋማት አክሲዮኖችን መግዛትና ከኩባንያው ዕድገት ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ ማስተማርና ማሳወቅ ይጠበቃል።

ስለዚህ አሁን ላይ ጊዜው ለኢንቨስተሮች የቁጠባ ጊዜ ሲሆን፤ ለአገልግሎቶች ደግሞ የዝግጁነት ጊዜ ነው። ስለዚህ ኩባንያዎች ገበያውን ለመምረጥ ሳይሆን የሚዘጋጁት ለራሳቸው የፋይናንስ ፍላጎት፣ የኮርፖሬት አደረጃጀታቸውን ለማሻሻል፣ ዋጋቸውን ለማሻሻልና ካፒታል በቀላሉ መሰብሰብ ሲያስችላቸው እሱን አጥንተው ወደ ገበያው ለመምጣት ይሆናል።

ለዚህ ዝግጅትም ድርጅቱ ድጋፍ እንደሚያደርግ የገለጹት ዶክተር ጥላሁን፤ በተለይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ከነበሩ አምስት ኩባንያዎች ተመርጠው በጋራ መሥራት እንደተቻለና ዝግጁነታቸውን ለማገዝም ድጋፍና ክትትል ሲደረግ እንደነበር አስታውሰዋል። አምስቱ የልማት ድርጅቶችም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ተቀጥያ የሆኑ መስራች ኩባንያዎች ሲሆኑ፤ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅትና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ናቸው።

የካፒታል ገበያ ሥርዓት ሲዘረጋ ዋና መርሆው ኢንቨስተሮችን የመጠበቅ ሥራ ነው የሚሰራው ያሉት ዶክተር ጥላሁን፤ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን በሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች መሠረት ለሕዝብ አክሲዮን እየሸጡ ያሉና ለሕዝብ የዕዳ ሰነድ እየሸጡ ያሉ ኩባንያዎች ማሟላት ያለባቸውን ሕግ የሚያወጣና የሚቆጣጠር እንደሆነ ነው ያስረዱት። ስለዚህ ተቋማቱ ወደ ኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን በመሄድ አክሲዮናቸውን ያስመዘግባሉ። ካስመዘገቡ በኋላም ገበያው ላይ አክሲዮኖቻቸውን የሚገበያዩ ኩባንያዎች ደግሞ ተጨማሪ የገበያው ሥርዓት የሚስቀምጣቸውን መረጃዎች ለገበያው ያቀርባሉ ሲሉ አብራርተዋል።

ለአብነትም ለሕዝብ አክሲዮን የሸጠ አንድ ኩባንያ የፋይናንስ ሪፖርት አያቀርብ ይሆናል። እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ግን በዋና ገበያ ላይ የተመዘገበ በመሆኑ ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ የፋይናንስ ሪፖርቶችን እንዲሰጥ እንዲሁም በዓመቱ መጨረሻ ደግሞ ኦዲትድ የሆነ የፋይናንስ ሪፖርት መስጠት ይጠበቅበታል። የእነዚህ እና መሰል ሕጎች ዋና ዓላማም ኢንቨስተሮች ስለ ኩባንያው የተሻለ መረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው ይህም ኩባንያዎችን የሚደግፍና የራሳቸውን የውስጥ አሠራር እንዲያሻሽሉ ያደርጋል ሲሉ አመልክተዋል።

ካፒታል ገበያ ባንኮችን፣ የንግድ ድርጅቶንችን እና መንግሥትን በማገናኘት እንደ አክሲዮን፣ ቦንዶች እና ተዋጽኦዎች ያሉ የተለያዩ የፋይናንሺያል መሳሪያዎችን በማውጣት እንዲሁም በመገበያየት የረጅም ጊዜ ገንዘብ የሚሰበስቡበት መድረክ ሆኖ የሚያገለግል ነው። በሌላ በኩል የባንክ ኢንዱስትሪው የኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት እንደመሆኑ በቁጠባና ተጠቃሚዎች እና በተበዳሪዎች መካከል ያለውን የገንዘብ ፍሰት በማመቻቸት፣ አስፈላጊ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በመስጠት የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚደግፍ እንደሆነ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያም በአሁኑ ወቅት ካፒታል ገበያ የተባለውን ትልቅ ፕሮጀክት ዕውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እያደረገች የምትገኘውም በዚሁ ምክንያት ነው።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎቹ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን የስቶክ ማርኬት አለመኖሩ በድርጅቶች መካከል ውድድርና ፈጠራ እንዳይዳብር ሆኗል፤ ስቶክ ማርኬትን ተግባራዊ ያደረጉ ሀገራት የውድድርና የፈጠራ አቅም ከፍተኛ ፍጥነት አለው። ስለዚህ ካፒታል ማርኬትን በሀገሪቱ ተግባራዊ በማድረግ ይጠበቃል። በተለይም የፋይናንስ ተቋማትና የተለያዩ ድርጅቶች ለዚህ ተግባር የመሪነቱን ሚና የሚወስዱ በመሆናቸው መንግሥትን ጨምሮ ከተቋማቱ ብዙ እንደሚጠበቅ ይታመናል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የጥቂቶች ጥፋት ለብዙዎች ክስረት

**ዋሰልኝ አየለ**

‹‹የከፋን ጎረቤት መብረቅ ይመታዋል›› የሚባል ሀገርኛ አባባል አለ:: ይህንኑ የሚያጠናክር ‹‹ለኃጥአን የወረደ ለጻድቃን ይተርፋል›› የሚባል ሌላም አባባል አለ:: የሁለቱም መልዕክት በአንድ መጥፎ ሰው ምክንያት የሚመጣ ጦስ ለበጎ ሰዎች ሁሉ ይተርፋል ለማለት ነው:: በተለይም ለጥፋተኛው የሚቀርቡ ሰዎች የጉዳቱ ሰለባ ይሆናሉ ማለት ነው:: ‹‹ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል›› የሚል ሦስተኛ አባባል መጨመርም ይቻላል::

ይህን ሁሉ ያስታወሰኝ አንድ ቀላል ገጠመኝ ነው:: አንድ ጓደኛዬ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ባመቻቸው ‹‹ኦንላይን›› ግብይት ዕቃ ገዛ:: ክፍያውን ከፈጸመ በኋላ ሌላ ተጨማሪ ዕቃ እንዲገዛ የሚያስገድድ ዘዴ ዘይደው አስገዙት:: ይህን ያደረጉት ጽሑፉን እንደገና አስተካክለው ነው:: የተስተካከለ (edited) ይላል:: የመጀመሪያውን ዕቃ ስለወደደው ሌላ ተጨማሪ ሊገዛ ከፈለ:: ችግሩ ግን ይህ ብቻ አልነበረም:: በሁለት ሰዓት ውስጥ ይደርሳል ያሉት ዕቃ በሁለት ሳምንትም ሳይደርስ መቅረቱ ነው:: ለጊዜው ቁርጡ ባይታወቅም የማጭበርበር አዝማሚያ ይመስላል:: ይህን የነገርኳቸው ሌሎች ጓደኞቼ እንደነገሩኝ ግን ቅድመ ክፍያ ከፍለው የተከዱ እንዳሉ ነገሩኝ:: በሌላ በኩል ደግሞ ታሽጎ የሚመጣው ዕቃ በኦንላይን የታየው እንዳልሆነ ያጋጠማቸው ነገሩኝ:: ኦንላይን ላይ የሚያሳዩት ሌላ፣ አምጥተው የሚያስረክቡት ሌላ (ጥራቱ የወረደ) ይሆናል:: እንዲህ አይነቶቹ አጭበርባሪዎች የሚጠቅሱት የአድራሻ ቦታ የውሸት ነው:: ከተጠቀሰው ቦታ ሲኬድ ምናልባትም እነርሱ ከሚሸጡት ጋር በፍጹም የማይገናኝ ሌላ ነገር ይሆናል::

እነዚህን ገጠመኞች ስሰማ አስቀድሜ ያዘንኩት በታማኝነት ለሚያገለግሉት የኦንላይን ነጋዴዎች ነው:: ምክንያቱም በእነዚህ አጭበርባሪዎች ምክንያት በአጠቃላይ የዘርፉ ስም ይጠፋል፤ የኦንላይን ግብይት ታማኝነት እንዲያጣ ያደርጋል:: የተጭበረበሩ ሰዎች እና ስለተጭበረበሩ ሰዎች የሚሰሙ ሰዎች ‹‹ኧረ ከኦንላይን አትግዛ›› ነው እንጂ የሚሉት ለይተው ከዚያ ካጭበረበረው ሰው ብቻ አይሉም:: ‹‹የከፋን ጎረቤት መብረቅ ይመታዋል›› ሆነ ማለት ነው:: ምክንያቱም በተመሳሳይ መስመር ላይ ያሉ ሰዎች እንደ ጎረቤት ነው የሚታዩት:: እንዲህ አይነት ማጭበርበሮች በዚያ ዘርፍ ላይ እምነት እንዳይኖር ያደርጋሉ::

ከሦስት ይሁን አራት ዓመታት በፊት በድላላ ሥራ ላይ በተሰማሩ አጭበርባሪዎች ላይ አንድ ትዝብት አጋርተን ነበር:: እነዚህ ደላሎች በየመብራት እንጨቱ ላይ ማስታወቂያ ይለጥፋሉ:: ከማስታወቂያው ግርጌ አድራሻ ይለጥፋሉ:: የሆነ ቦታ ቢሮ ተከራይተው ለትንሽ ጊዜ ከዚያ ቢሮ ሆነው ሥራ ፈላጊዎችን ይመዘግባሉ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ቢሮውን ይለቁታል:: ገንዘብ የሚያስከፍሉት በቅድሚያ ነው:: የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በእነዚህ አጭበርባሪዎች ላይ የሰራውን ዘገባ አስታውሳለሁ:: ጋዜጠኛው ሥራ ፈላጊ መስሎ ሲደውልላቸው ትክክለኛውን ነገር አይናገሩም፤ ሁሉም ነገር የሚሆነው ቢሮ መጥተህ ነው የሚል መልስ ይሰጣሉ:: እኔም ከአንድ ጓደኛዬ ጋር አራት ኪሎ ከጠቆሙት አንድ ቢሯቸው ውስጥ ገብተን አረጋግጠናል:: በር ላይ ሆኖ ይህን የሚከላከልና የሚቆጣጠር ሰው አለ:: አፋጠን ስንጠይቀው ሲጨናነቅ ነበር:: እንግዲህ በእነዚህ አጭበርባሪዎች ምክንያት በደፈናው ‹‹ደላላ›› በሚል የብዙ ታማኝ ደላሎች ስም አብሮ ይጠፋል ማለት ነው:: ድለላ የሚለው ስም ከማጭበርበር ጋር የተያያዘ ትርጉም ይይዛል ማለት ነው::

የኦንላይን ግብይት ቴክኖሎጂ የወለደው ሥራን ያቀለለ የሥልጣኔ መገለጫ ነው:: አንድ ሰው ጊዜ ሳያባክን የሥራ ቦታው ላይ የሚፈልገው ነገር ይመጣለታል:: ይህን የመሰለ ሥልጣኔ ግን ጥቂቶች ጭቃ ሊቀቡት ነው ማለት ነው:: ሰዎች አምነው ላይገዙ ነው ማለት ነው:: በእርግጥ የግድ ሁሉም ክፍያ ቅድሚያ አይሆንም:: ዕቃውን ከተቀበሉ በኋላ መክፈል ይቻላል:: ይህ ሲሆን ግን ሻጮችም እዚያ ድረስ ለፍተን ‹‹አልገዛም›› ቢለን የሚል ስጋት ያድርባቸዋል:: እንዲህ የሚል (አልከፍልም የሚል) አይኖርም ማለትም አይቻልም:: ምክንያቱም መተማመን የጠፋው ከሁሉም ወገን ነው::

እጅግ አደገኛው የኋላቀርነት መገለጫ ስርቆት፣ ማታለልና ማጭበርበር ነው:: ይህን የሚቆጣጠር የሰለጠነ የተዘረጋ ሥርዓት እንኳን ባይኖረን ‹‹ኩሩ ኢትዮጵያዊነት›› እያልን የምንፎክርበት ሞራላችን ግን ሊኖር ይገባ ነበር:: ምክንያቱም ከየትኛውም ዘመናዊ የረቀቀ ቴክኖሎጂ በላይ ሞራል ይበልጣል:: የሰለጠኑት ሀገራት ግን ሁለቱንም አላቸው::

ጋዜጠኛና ደራሲ በረከት በላይነህ ሰሞኑን በአንድ የፖድካስት ሚዲያ ላይ ሲናገር የሰማሁት ገጠመኝ ብዙ እንድገረም ያደረገኝ ነው:: ጓደኛው ያጋጠመው ነው:: ነገሩ እንዲህ ነው::

አንድ ጓደኛው ወደ ሀገረ ቻይና ተጉዞ ነበር:: ያረፈበት ቤት ውስጥ ዕቃ (ስልክ መሰለኝ) ረስቶ ይሄዳል:: የተሰረቀ መስሎት የሄደበት አካባቢ ለሚገኝ የፀጥታ አካል አመለከተ:: እዚያው ቆሞ እያለ የሚያዩትን አይተው (በአሰራራቸው ሥርዓት) ዕቃው ቻይና ምድር ላይ እንዳልጠፋ፣ ይልቁንም ያረፈበት ክፍል ውስጥ እንዳለ ነገሩት:: ‹‹እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል? እንዳልጨቃጨቃቸው ሊገላገሉኝ ፈልገው ነው እንጂ!›› እያለ ወጣ:: ወደ ክፍሉ ሲገባ ግን የጠፋበት የመሰለው ዕቃ እንዳስቀመጠው ነው:: መቼም በዘረጉት ሥርዓት እንጂ በአስማት ሊሆን አይችልም ብሎ እየተገረመ ወደ ሀገሩ መጣ::

ችግራችን ድህነት ነው እንዳይባል የማጭበርበርና የማታለል ድርጊቶች የሚፈጸሙት የተሻለ የገቢ ደረጃ ባላቸው ነጋዴዎች ነው:: በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩ ሰዎች ሀቀኞች ናቸው:: የጽዳት ሠራተኞች ‹‹ወድቆ ያገኙትን ይህን ያህል ሺህ ብር አስረከቡ›› ሲባል በተደጋጋሚ እንሰማለን:: የሚጠየቁበት የህግ አግባብ ባይኖር እንኳን ለፈጣሪያቸው ግን ታማኝ ናቸው:: የእነርሱ ዳኛ ህሊናቸው ነውና ማንም ስላላየኝ የራሴ ላድርገው አይሉም:: የተሻለ ገቢ አለው የሚባለው አካል ግን ሊያስጠይቀው የሚችል ማስረጃና መረጃ እያለ ሁሉ ልማድ ሆኖበት ያጭበረብራል:: ነጮች ጥቁሮችን የሚጠሉበት አንዱ ምክንያት እንዲህ አይነት ኋላቀርነት ነው:: እንዲህ አይነቱን የኋላቀርነት ልማድ ሳያስወግዱ ‹‹ኩሩ ጥቁር ነኝ! ኩሩ ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ ኩሩ አፍሪካዊ ነኝ...›› ማለት ከንቱ ውዳሴ ነው:: ምንም እንኳን ድርጊቱ የጥቂቶች ቢሆንም ሲደጋገም ግን እንደ ሀገር ብዙ ችግር እንዳለብን ያሳያል::

ሞራል ያላቸው ሰዎች እንዳሉ ግልጽ ነው:: ያም ሆኖ ግን ከስንዴ ውስጥ እንክርዳድ አይጠፋምና በጥቂቶች ገጽታ እንዳይበላሽ ህጋዊ ቁጥጥር መደረግ አለበት፣ ግለሰቦች አጭበርባሪ ሲያጋጥማቸው ሊያጋልጡ ይገባል:: ‹‹ብናጋልጥ ምን ዋጋ አለው!›› የሚል ተስፋ መቁረጥ እንዳይኖር የፀጥታ አካላትም ጥቆማ ሲሰጣቸው ተገቢውን ትኩረትና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል:: ምክንያቱም የእንዲህ አይነት ጥቃቅን ነገሮች ድምር የሀገርን ገጽታ ያበላሻል!

# ዓለም አቀፍ



## በደቡብ አፍሪካ አንድ ሕንፃ ተደርምሶ በርካቶች መውጫ አጥተዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በደቡብ አፍሪካ በግንባታ ላይ ያለ አንድ ሕንፃ ተደርምሶ አራት ሰዎች ሕይወታቸው ሲያልፍ በርካቶች መውጫ ማጣታቸው ተነገረ።

በሕንፃው ውስጥ መውጫ ያጡ 51 ሰዎችን ሕይወት ለመታደግ የነፍስ አድን ርብርብ መጀመሩም ተገልጿል።

በዌስተርን ኬፕ ግዛት በምትገኘው ጆርጅ ከተማ በደረሰው የሕንፃ መደርመስ አደጋ 24 ግለሰቦችን ከፍርስራሹ በማውጣት ወደ ሆስፒታል መውሰድ ተችሏል።

ሕንፃው ሰኞ እለት በተደረመሰበት ወቅት 75 ሠራተኞች ነበሩ።

በባህርዳርቻዋ ከተማ የደረሰውን ክስተት መንስኤ ለማጣራት ምርመራ ተጀምሯል ተብሏል።

ሕንፃው በሀገሬው ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ገደማ እንደተደረመሰ የዌስተርን ኬፕ አስተዳዳሪ አላን ዊንዴ ገልጸዋል።

ከኬፕታውን በስተምሥራቅ 450 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ከተማ ውስጥ ከደረሰው የመደርመስ አደጋ ሰዎችን በሕይወት ለመታደግ የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች ወደ ስፍራው ሲጣደፉ ታይተዋል።

ከፍራስራሾቹ ውስጥ ከነበሩት 22 ሰዎች መካከል ሁለቱ ወዲያውኑ ሕይወታቸው አልፏል። በኋላም ሌሎች ሁለት በደረሰባቸው ጉዳቶች ምክንያት ሕይወታቸው እንዳለፈ ተዘግቧል።

“በዚህ አደጋ ሕይወታቸውን ላጡ ቤተሰቦች መጽናናትን እየተመኘን እየተጠባበቁ ላሉ ቤተሰቦች በሃሳብ ከናንተ ጋር ነን” ሲሉ የከተማዋ ከንቲባ አንድ ቫን ዋይክ ተናግረዋል።

ከ100 የሚበልጡ የነፍስ አድን ሠራተኞች ከአነፍናፊ ውሾች ጋር ተሣማርተው ከሕንፃው ፍርስራሽ ሰዎችን ለማውጣት ሌሊቱን ሙሉ ሲሠሩ ነበር ተብሏል።

ይህንን ሥራ ለማገዝ ዘመናዊ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተነግሯል።

በፍርስራሹ ውስጥ ተቀብረው ከሚገኙ ሰዎች ውስጥ ከተወሰኑት ጋር ንግግር ማድረግ እንደተቻለ ባለስልጣናቱ አስታውቀዋል።

ሕንፃው ሙሉ በሙሉ ተደርምሶ ፍርስራሾች ብቻ የሚታዩበት ፎቶዎች ወጥተዋል።

“አንድ ግለሰብ በሕንፃው ላይ ሲሠራ አየሁ። ከዚያም ሕንፃው ሙሉ በሙሉ ሲደረመስ አየሁ። በጣም ደንግጫለሁ። በጣም ያሳዝናል ”ሲሉ ቴሬሳ ጄይ የተባሉ የአካባቢው ነዋሪ ለሮይተርስ መናገራቸው ተዘግቧል።

## ለ10 ዓመት ኮማ ውስጥ የቆየ ባሏን የተንከባከበች ባለቤቱ የጥንካሬ ተምሌት ተብላለች

በቻይና ለ10 ዓመታት ኮማ ውስጥ የነበረውን ግለሰብ ስትንከባከብ በመቆየቷ ሲነቃ ከተመለከተች በኋላ ባለቤቱ የጥንካሬ ተምሳሌት ተብላ በቻይና እየተወደሰች ይገኛል።

በምሥራቃዊ ቻይና አንሁይ በተባለችው ግዛት ነዋሪ የሆነችው ሰን ሆንግሻይ ባሏ እ.አ.አ. በ2014 በገጠመው ድንገተኛ የልብ ድካም ኮማ ውስጥ ይገባል። በአጭር ጊዜ ከኮማ ይወጣል፤ የቤተሰቡም ስጋት ይወገዳል ተብሎ ቢጠበቅም ምን እየተካሄደ እንደሆነ በውል መረዳትና መግለጽ የማይችለው ባል 10 ዓመታት ኮማ ውስጥ ይቆያል።

ከሰሞኑ ግን ሰን ለድፍን10 ዓመታት በተስፋ የጠበቀችው፤ በብዙ የደከመችለት ጉዳይ ፍሬ አፍርቶ የምትወደውና የሁለት ልጆቿ አባት ነቅቷል። ያለፉትን ዓመታት እንዴት እንዳሳለፈች በእንባ ታጅባ ስትነግረው የሚያሳይ ምስልም ተለቋል።

“ምንም እንኳን በጣም ቢደክመኝም ቤተሰባችን ወደቀድሞው ደስታው እንዲመለስ የተከፈለ መስዋዕትነት አድርጌ እወስደዋለሁ” ስትልም ዳዋን ለተሰኘው የቻይና መገናኛ ብዙኃን ተናግራለች።

የሰን ባል ረጅም ዓመት ኮማ ውስጥ መቆየቱን ተከትሎ የሚስቱ ድጋፍ እጅግ ወሳኝ ነበር። የሰውነት አካሉን ማዘዝ ስለማይችል አይንቀሳቀስም፤ ይህም ካለሚስቱ ድጋፍ መጸዳዳት እንኳን እንዳይችል አድርጎታል።

ዓይኑ በሂደት በከፊል መገለጥ መጀመሩ ተስፋዬን እያለመለመው ሄደ የምትለው ሰን፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሕመሙ እየበረታ ፈተናዋን ቢያበዛባትም እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ አብራው ለመቆየት ቃል ለገባችለት ባሏ ሙሉ ጊዜዋን ሰጥታ ያለመሰልቸት ተንከባክባዋለች።



የ84 ዓመቱ የታማሚው አባትም የዚህ ምስክር ናቸው። “ሰን የልጄ ሚስት ብትሆንም ከሴት ልጄ የተሻለች ልዩ ሰው ናት፤ ከእርሷ ጋር ማንም አይወዳደርም” ሲሉ ለልጃቸው ያሳየችውን ወደር የለሽ ፍቅር እና እንክብካቤ አድንቀዋል ብሏል ሳውዝ ቻይና ሞርኒንግ ፖስት በዘገባው።

ከኮማ ከወጣ ባሏ ጋር የተነሳችው ምስልም በቻይና ማህበራዊ ሚዲያዎች በስፋት እየተዘዋወረ ነው።

# የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሊቅ

ክብረአብ በላቸው



በተሰማሩበት የሙያ መስክ የላቀ አበርክቶ በማኖር የሀገራቸውን ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስጠሩና ታሪካቸውን በደማቅ ቀለም ማፃፍ የቻሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ቀላል አይደለም። ከእነዚህ እንቁ ግለሰቦች መካከል ታላቁ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሊቅ ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ አንዱ ናቸው።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ከአባታቸው ግራዝማች ከበደ አድነውና ከእናታቸው ወይዘሮ ፋንታዬ ነከሬ ግንቦት 8 ቀን 1930 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። የሙዚቃ ፍቅርን ገና በልጅነታቸው ያሳደሩባቸው እናታቸው ቢሆኑም ታዳጊው አሸናፊ ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳሉ ወላጅ እናታቸውን በሞት አጥተዋል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ መሠረታዊ ትምህርታቸውን በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት እና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (አሁን ኮከበ ጽባሕ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚባለው) ካጠናቀቁ በኋላ ከሐረር የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ተመርቀዋል። ከዚያም ወደ አሜሪካ በማቅናት ኒውዮርክ ከተማ ከሚገኘው ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሮቸስተር፣ ኢስትማን የሙዚቃ ትምህርት ቤት (University of Rochester's Eastman School of Music) በ1954 ዓ.ም በመጀመሪያ ዲግሪ ከተመረቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትን መሥርተዋል።

የትምህርት ቤቱም የመጀመሪያው ዳይሬክተር ከመሆናቸውም ባሻገር ሙዚቃን በማስተማር አገልግለዋል። በተጨማሪም በአዲስ አበባ የወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር (ወ.ወ.ክ.ማ.)፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የበጎ አድራጎት ድርጅት መርሐ-ዕውራን ትምህርት ቤት እና በመሳሰሉ የወጣቶች ማኅበራት እየተገኙ የሙዚቃ ትምህርት ይሰጡ ነበር።

የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ሆነው ከ 1955ዓ.ም እስከ 1960 ዓ.ም ድረስ ባገለገሉበት ወቅት በንጉሠ ነገሥቱ "ብሔራዊ የሙዚቃ አቀናባሪ" ተብለው ከመሠያማቸውም ሌላ ለባሕላዊ ጉዳዮች ላደረጉት የላቀ ተዋጽኦ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት ተሸላሚ ሆነዋል። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልደት በዓል በተከበረበት በዚሁ ወቅት በሀንጋሪያ መንግሥት ተጋብዘው ወደ ቡዳፔስት በመጓዝ ታዋቂውን «እረኛው ባለዋሽንት» እና «የኢትዮጵያ ሲንፎኒያ" የተባሉትን ሁለት ድርሰቶቻቸውን በአቀናባሪነትና በኦርኬስትራ መሪነት አቅርበው፤ በሽክላ አሳትመዋል። መታሰቢያነቱንም ለጃንሆይ የልደት በዓል አበርክተዋል። ከሸክላው የሚገኘውን ገቢ በወቅቱ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሥር ይተዳደር ለነበረው የመርሐ-ዕውራን ትምህርት ቤት ለግሠዋል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ 'ጥቁሩ ኮዳሊ' የሚለውን ማቆላመጫም ያገኙት የረቂቅ ሙዚቃ ድርሰታቸውን በሀንጋሪ ውስጥ ከ'ፊልሃርሞኒክ ኦርኬስትራ ጋር በእርሳቸው ሙዚቃ መሪነት ባቀረቡበት ጊዜ ነበር። ታሪኩ እንዲህ ነው፡- እ.ኤ.አ 1967 ዓ.ም. በቡዳፔስት ሃንጋሪ ታላላቅ አውሮፓውያን የሙዚቃ አቀናባሪዎች የሙዚቃ ሥራዎቻቸውን ባቀረቡበት አዳራሽ ውስጥ አንድ አዲስ ክስተት ታየ፡፡ ይኸውም በዚያ የነበረውን የአውሮፓ የሙዚቃ ኦርኬስትራ ለመምራት ቆሞ የነበረው ከአህጉረ አፍሪካ የ26 ዓመቱ ኢትዮጵያዊ ወጣት አሸናፊ ከበደ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ወጣት የሙዚቃ አቀናባሪ በሚያስደንቅ ሁኔታ ቅንብሩን ከመምራቱ የተነሣ በጊዜውና በቦታው የነበሩት ነጭ ተመልካቾች፡- «አንድ ጥቁር አፍሪካዊ በሙዚቃ ትምህርት የሠለጠኑትን የነጮች ኦርኬስትራ እንዴት ሊመራ ቻለ?» በማለት አድንቀው ነበር፡፡

የመጀመሪያውንና ታላቅ የሆነውን እረኛው ባለዋሽንት" የሚለውን ቅንብሩን በይፋ ካቀረበ በኋላ የፕሮፌሰር አሸናፊ ዝና በመላው ሃንጋሪ ናኘ፤ ሃንጋሪያውያን በሀገራቸው ታዋቂ ከነበረውና እ.አ.አ ከ 1882 –1967 ዓ.ም. ከኖረው ዞልታን ኮዳሊ ከተባለው የሙዚቃ አቀናባሪ ጋር በማመሳሰል «ጥቁሩ ኮዳሊ» የሚል ስም ሰጡት። ፕሮፌሰር አሸናፊ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የዓለም አቀፍ የሙዚቃ ትእይንቶች ላይ ተገኝተዋል በተለይም በ1960ዎቹ አካባቢ በርካታ ሙዚቃዎችን አቀናብረዋል፤ ኦርኬስትራዎችንም መርተዋል።

በተጨማሪም ስለ ሦስተኛው ዓለም ሀገሮች፣ ስለ ዐረብ፣ ስለ ጃፖንና ስለ አውሮፖ ሙዚቃ ከነበረው ጥልቅ ዕውቀት የተነሣ በሙዚቃ ጥበብ ሚዩዚኮሎጂ/ ታላቅ ሰው ለመባል በቅተዋል፤ በዚህም ምክንያት ታላላቅ የሙዚቃ ሰዎችንና ሥራዎቻቸውን ይዘው በሚወጡ ጽሑፎች ላይ ስማቸው ተጽፏል፡፡ በ(International Who is Who In Music 1.0.9 ) ከአፍሪካውያንና አፍሪካ አሜሪካውያን ታዋቂ ሙዚቀኞች ተርታ ሳይቀር አንዱ ሆነው ተቆጥረዋል።

ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካ በተመለሱ ጊዜ የሙዚቃ ጥናታቸውን አጠናቀው፣ በሁለተኛ ዲግሪ በ1960 ዓ.ም፤ በዶክትሬት ደግሞ በ1963 ዓ.ም ከ 'ዌስሊያን ዩኒቨርሲቲ' ተመረቁ። ከ 1962 ዓ.ም እስከ 1968 ዓ.ም ድረስ በኒው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ፣ 'ክዊንስ ኮሌጅ' እና በማሳቹሴትስ ብራንዲስ ዩኒቨርሲቲ በረዳት ፕሮፌሰርነት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ ለአሥራ ዘጠኝ ዓመታት በፍሎሪዳ ዩኒቨርሲቲ፤ መጀመሪያ በፕሮፌሰርነት በኋላም የዩኒቨርሲቲው "የጥቁር አሜሪካውያን የባህል ማዕከል" ዳይሬክተር በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተዋል። በተጨማሪም በዶክተር መላኩ በያን የተመሠረተውን "የኢትዮጵያ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር ድርጅት" ዳይሬክተር በመሆን አገልግለዋል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከሙዚቃ አቀናባሪነታቸውና ከኤትኖሚ ዚኮሎጂስትነት ባሻገር የፈጠራ ፀሐፊም ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ከሥራዎቻቸው መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀስለትና በ1964 ዓ.ም. የታተመው "Confession" የተባለው ድርሰት ሀያስያንን በመማረክ የአፍሪካ ደራስያን፣ አራቱ የአፍሪካ ሥነ ጽሑፎች (Hour frican Literature) በሚሏቸው ኅትመቶች ውስጥ ተካቶ ሊጻፍ በቅቷል፡፡

ከዚህም ባሻገር የተለያዩ ሥራዎቹን ማለትም ከሙዚቃ ጋር የተያያዙ መጣጥፎችን፣ በዓለም ሙዚቃ ላይ የጻፋቸውን መጽሐፎቹን ጨምሮ ለኅትመት አብቅተዋል፡፡ ሙዚቃ ነክ ከሆኑት ሥራዎቹ መካከል እ.ኤ.አ በ1966 ዓ.ም የሙዚቃ ሰዋሰው፣ የአምባራስ የአዝማሪ ሙዚቃ በ1969 ዓ. ም. ፣ የአፍሪካ ሙዚቃ በምዕራቡ ዓለም በ1972 ዓ. ም. "The Bon-Lyre of North East Africa. Kirar. The Devil's instrument" በ 1977 ዓ.ም ሙዚቃ በጥቁር አይሁዶችና በክርስቲያን ማኅበረሰብ፣ በ 1980 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ዘመናዊና ባህላዊ ሙዚቃ ሂደት፣ በ1976 ዓ. ም. የጥቁሮች ሙዚቃ ሥረ መሠረት፣ የአፍሪካውያንና የጥቁር አሜሪካውያን የሙዚቃ መሣሪያ ዓይነቶችንና ውዝዋዜዎችን የዳሰሰባቸው የጽሑፍ ሥራዎችና የኢትዮጵያ ሙዚቃ ዘመናዊ አባባሎችና ግጥሞችን ለሕትመት አብቅተዋል፡፡ ከ 8 የሚበልጡ ዋና ዋና የሙዚቃ ሥራዎችንም አቀነባብረው አበርክተዋል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ / Febri Sbolar/ የሚል የምሁርነት ስያሜ የተሰጣቸው ሲሆን የተለያዩ ሽልማቶችንም አሸንፈዋል። ለምሳሌ፡- UNESCO Florida Finc - Mrs Couns, Na fional Endowment for the Humanist, Canada National Music Counsel, American Learned Society Counsel 0-9 UNESCO Research Grant ሽልማቶችን ተቀብለዋል፡፡

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከሙዚቃ ድርሰቶቻቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂነትና ተወዳጅነትን ያተረፈው 'እረኛው ባለዋሽንት' ብቻ ሳይሆን ከሌሎቹም አንዳንዱን ለመጥቀስ፡- 'ሰላም ለኢትዮጵያ'፤ 'የሀገራችን ሕይወት'፤ 'የተማሪ ፍቅር'፤ 'እሳት እራት'፤ 'ኮቱሬኽያ' እና 'ኒርቫኒክ ፋንታሲ' የሚባሉት ድርሰቶች የሚጠቀሱ ናቸው። በሥነ-ጽሑፍ ረገድ ደግሞ በተማሪነታቸው ዘመን በ1956 ዓ.ም የደረሱት እና ያሳተሙት "ንስሐ" ወይም Confessions የተባለው መጽሐፍ እና "የሙዚቃ ሰዋሰው" እንዲሁም በርካታ የጥናትና ምርምር ድርሰቶች ይጠቀሳሉ።

የፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ዋና ጥረት የነበረው በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያሉ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን የወከለ አንድ ዓይነት የሆነ የሰው ልጆችን ማንነት የሚገልጽ የሙዚቃ ቅንብርን አግኝቶ በእርሱ አማካኝነት ኪነ ጥበብን መግለጽ ነበር፡፡ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ላይ በዓለም ውስጥ ለሚታየው የዘር ግጭትና መድሎ እንዲሁም ማኅበራዊ ኢ-ፍትሓዊነት መፍትሔ የሚሆንን ነገር በሙዚቃው ውስጥ ይፈላልግ ነበር።

ፕሮፌሰር አሸናፊ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሙዚቃ አቀናባሪነታቸው ይልቅ በምሁርነታቸው በመምህርነታቸው የበለጠ ይታወቃሉ። በሙዚቃው ቅንብር ከዓለም አቀፍ መርሆች ይልቅ በራሳቸው ፈጠራ ላይ ያተኩራሉ። ከዚህ የተነሣም ምዕራባውያን ባስቀመጡት የሙዚቃ ምድብ ሊፈረጁና ደረጃቸው ሊታወቅ አልቻለም፡፡

በተጨማሪም ፕሮፌሰር አሸናፊ የኢትዮጵያ ሙዚቃ በአውሮፖ የሙዚቃ መሣሪያዎች እንዲዳብርም አድርገዋል። በጣም የሚወዷቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ ለምሣሌ፡- ዋሽንትን፣ ክላርኔትንና ቫዬሊንን በመጠቀምና የኢትዮጵያን ዜማ በማስገባት አስደናቂ ኢትዮጵያዊ ዜማዎችን ለመፍጠር ችለዋል። ለምሣሌ «እረኛው ባለዋሽንት» እና አራቱ ዋና ዋና ሥራዎቹን ጨምሮ ኮቶ ዚተር በሚባል ባለ13 ክር መሳሪያ ክላርኔት ወይም ፍሉትና ቫዬሊን በመጠቀም የተጫወቷቸው ናቸው፡፡

ይህ የኢትዮጵያን ዜማ ከምሥራቅና ከምዕራብ የሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር በመቀላቀል በሙዚቃ ዓለም አቀፋዊነትን የፈጠረ ሲሆን፣ በዚህ ሥራቸውም ሁለቱንም የዓለም ሥራ ማለትም ምሥራቁንና ምዕራቡን ሊያስደንቅ ችሏል። በዚሁ ሙያ በቆዩበት ዘመን ሁሉ ለትውልድ ሀገራቸው ለኢትዮጵያና እንዲሁም ለጃፖን፣ ለመካከለኛው ምሥራቅ ፤ ለህንድ ፣ ለምሥራቅ አውሮፖ፣ በተለይም ለሀንጋሪና ለአሜሪካ ሙዚቃ የተለየ ትኩረት ነበራቸው።

የፕሮፌሰር አሸናፊ የሙዚቃ ቅንብሮች ውስጣዊ ስሜትን የሚፈጥሩትን ያህል በውጫዊ ነገሮችም ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ ለምሣሌ አንዳንድ ቅንብሮቹ በማኅበረሰብ፣ በፖለቲካና በመንግሥት ላይ ያተኮሩ ሲሆን ከፊሎቹ ደግሞ በቀጥታ ከሙዚቃና የሙዚቃን ቅንብር ከመተወን ጋር ይያያዛሉ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው።

እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ እና በ1970ዎቹ በነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታት ጫና የተነሣ የግጥምና የዜማ ይዘቶች ፖለቲካውንና ርእዮተ ዓለሙን በሚደግፉበት መልኩ እንዲደርሱ ይደረግ ነበር፡፡ ከነበረው ጫና የተነሣ የፕሮፌሰር አሸናፊ የግጥምና የዜማ ድርሰቶች ውጫዊ ይዘታቸው ባለሥልጣናቱ እንደሚፈልጉት ቢመስሉም በውስጣቸው ግን ድብቅ ምስጢርን ያዘሉ እንዲሆኑ ስለማድረጋቸው ይነገራል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ፍሎሪዳ ውስጥ በሚገኘው የታለሀሴ ዩኒቨርስቲ በአፍሪካ አሜሪካ የባህል ማዕከል በዳይሬክተርነት በቆዩበት ጊዜ፣ የአፍሪካንና የአፍሪካ አሜሪካንን ዳንስ፣ ሙዚቃ እና ድራማ በፍሎሪዳ ከተማ እንዲታይ ያደርጉ ነበር፡፡ ፕሮፌሰር አሸናፊ ከታላቅ የሙዚቃ አቀናባሪነታቸውም በላይ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው አስተማሪ ነበሩ።

እርሳቸው በነበሩበት ኮሌጅ ውስጥ የሙዚቃ አስተማሪ የነበረች አንዲት ሴት ስለ ፕሮፌሰር አሸናፊ በተማሪነቷ ጊዜ ስለነበራት ትውስታ ስትናገር፣ «እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ ውስጥ ሙዚቃ በሚያስተምረን ወቅት ምርምር ያሠራን ነበር። ከክፍል በፊትና በኋላ የአፍሪካ ሙዚቃ እንሰማለን። ከተዛባ አመለካከታችን የተነሣ ቀድሞ እንጠላው የነበረውን የአፍሪካ ሙዚቃ መውደድ ጀመርን። ከዚህም የተነሣ የጥቁር አፍሪካ፣ የእስያንና የዐረቡ ዓለም ሙዚቃዎች በኮሌጁ የኮርስ ዝርዝር ውስጥ ተካተቱ፡» የሚል ምስክርነት ሰጥታለች።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ግንቦት 1 ቀን 1990 ዓ.ም በ 60 ዓመታቸው በታለሃሴ ፍሎሪዳ ዩኒቨርሲቲ በማገልገል ላይ እያሉ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ፕሮፌሰር አሸናፊ ከመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ባለቤታቸው (ወይዘሮ እሌኒ ገብረመስቀል) እና ከሁለተኛ አሜሪካዊት ባለቤታቸው አራት ልጆችን (ሦስት ሴቶችና አንድ ወንድ) ልጆችን አፍርተዋል። ፕሮፌሰር አሸናፊ ጥንታዊውን ኢትዮጵያዊ ባለቅኔና የሙዚቃ አቀናባሪ የነበረውን ቅዱስ ያሬድን የሚያደንቁ የሚወዱ ከመሆኑ የተነሣ ከአሜሪካዊት ሁለተኛዋ ባለቤታቸው ከዶክተር ሜትኮዊክስ የወለዱትን ልጃቸውን ስም ያሬድ ብለው ሰይመውታል።

እኛም እኚህን የኢትዮጵያ ሙዚቃ ባለውለታና በዘርፉ ሀገራቸውን በከፍተኛ ክብር ማስጠራት የቻሉትን ሰው ነፍስ ይማር እንላለን።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ
ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የሲዳማ ክልልን አትሌቲክስ የማጠናከር ጥረት

**ዓለማየሁ ግዛው**

ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ስፖርት በአህጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ ታሪካዊ ድሎችን በማስመዝገብ ግንባር ቀደምና የውድድር አድማቂ ከሆኑ ሀገራት ተርታ ትመደባለች:: ለአትሌቲክስ የሚያመች የአየር ንብረትና መልከዓ ምድራዊ አቀማመጧ ደግሞ ለዚህ ተጨማሪ አቅምን ፈጥሮላታል:: ለስፖርቱ አመቺ ተፈጥሮን በመታደላቸው እምቅ አቅም ካላቸው ክልሎች መካከል በቅርቡ የተቋቋመው ሲዳማ ክልል ይጠቀሳል::

በርካታ የሩጫ እና የሜዳ ተግባራት ላይ ተሳታፊ በመሆን ሀገርን ያስጠሩ አትሌቶችንም ይኸው ክልል አፍርቷል:: አትሌት ቁርቦ ቱሞ እና በላይነህ ዴንሳሞን የመሳሰሉ አንጋፋዎችንም መጥቀስ ይቻላል:: ይሁንና ካለው አመቺ የአየር ንብረትና የመልክዓ ምድር አቀማመጥ አንጻር እምቅ አቅሙን አውጥቶ በመጠቀም ላይ ነው ተብሎ አይታመንም:: በመሆኑም ክልሉ አቅሙን አውጥቶ በሀገር አቀፍ ውድድሮች ውጤታማ ተሳትፎን ለማድረግ አቅዶ እየሰራ መሆኑን ስፖርቱን በበላይነት የሚመራው የክልሉ ፌዴሬሽን አስታውቋል:: በክልሉ ሁለት ትልልቅ ክለቦች (ሲዳማ ቡና እና ሲዳማ ፖሊስ) እንዲሁም ክለቦቹን ሊመግቡ የሚችሉ በብሄራዊው ፌዴሬሽን እና በክልሉ ስፖርት ኮሚሽን የሚደገፉ የስፖርት ማዕከላትና ፕሮጀክቶችም ይገኛሉ::

ለስፖርቱ ውጤታማነት ትልቁን ድርሻ የሚወስደውን የፕሮጀክቶች ስልጠና ለማጠናከር እንዲሁም ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን በማደራጀት ከትምህርት ቤቶች ጋር የማቆራኘት ስራዎችም ተጀምረዋል:: በስራቸው 500 የሚሆኑ ታዳጊዎችን አቅፈው የሚገኙ 18 ፕሮጀክቶች ሲኖሩ፤ በክረምት መርሃ ግብር የተደራጁ 12 ተጨማሪ ፕሮጀክቶችም ይገኛሉ:: ከነዚህም በተጨማሪ በቀጣይ እንደ አዲስ የሚደራጁ ፕሮጀክቶች ከስፖርት ምክር ቤቱ ጋር እንዲተሳሰሩ የማድረግ ስራዎችም እየተከናወኑ ነው::

ስፖርቱ በዘላቂነት ውጤታማ ተሳትፎ እንዲኖረው የማዘውተርያ ስፍራ ያለው ሚና ትልቅ ሲሆን፣ ክልሉም ከትምህርት ቤቶች፣ ከወረዳዎች እና ከዞኖች ጋር አስተሳስሮ ስፖርቱ የሚፈልገውን ምቹ አካባቢ ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ችሏል:: በቀጣይ እነዚህን አጠናክሮ ለማስቀጠል እና ውጤታማ ተሳትፎን ለማድረግ ለአሰልጣኞች ስልጠና የመስጠት፣ ደረጃቸውን ማሻሻል እና የአቅም ግንባታን ለማድረግም ታቅዷል:: ፌዴሬሽኑ በዚህ ዓመት ለ85 ዳኞችና አሰልጣኞች የአቅም ግንባታና የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት ችሏል::

በተለያዩ የእድሜ እርከኖች በክልል እና ሀገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ውድድሮች ተሳትፎ እያደረገ የሚገኘው ክልሉ የተሻለ ውጤት ቢያስመዘግብም የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሱን የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ አስራት አሰፋ ይናገራሉ:: በሀገር አቀፍ ውድድሮች ውጤታማ ተሳትፎን የሚያደርግ እንዲሁም ጠንካራ ስፖርተኞችን ለሀገር ማፍራት የሚችል የክልል ፌዴሬሽን ለመፍጠር በእቅድና በተግባር በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል:: ክልሉ ሶስት ዓይነት የአየር ንብረቶች ያሉት በመሆኑ ለሁሉም የስፖርት ዓይነቶች የተመቸ ቢሆንም፤ ለአትሌቲክስ ስፖርት ደግሞ ይበልጥ ተመራጭ ነው:: ይህንኑ ጸጋውን በመጠቀምም የክልሉን አትሌቲክስ ስፖርት ተሳትፎ ውጤታማ ለማድረግ መስራት አስፈላጊ ነው::

ፌዴሬሽኑ በቀጣይ ዓመታት ለስፖርቱ ተሳትፎና ውጤታማነት ምን መስራት እንደሚኖርበት ለይቶ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል የስፖርቱን እንቅስቃሴ በውጤታማነት ለመምራት የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን ማጠናከርና ማስፋት አንዱ ነው:: ከአበረታች ቅመሞችና ከዕድሜ ማጭበርበር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ለስፖርት ቤተሰቡ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥና የአቅም ግንባታ ስራዎችን አጠናክሮ መስጠት፣ የውስጥ ውድድሮችን በማብዛትና በማጎልበት የፕሮጀክቶችን አቅም አሳድጎ በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤታማ ተሳትፎ ማድረግም የእቅዱ አካል ናቸው:: ከክልሉ ስፖርት ኮሚሽንና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፣ ስፖርቱን ህዝባዊ መሰረት ለማስያዝና ተጨማሪ ክለቦችን ለማቋቋምም በመንቀሳቀስ ላይ እንደሆኑም ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል::

በክልሉ የሚካሄዱ ሀገር አቀፍ ውድድሮች የክልሉን የአትሌቲክስ እንቅስቃሴ ከማሳደግ አኳያ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል:: ለውድድር የሚመጡት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ትልቅ ልምድን ለመለዋወጥ ስለሚጠቅሙ ተጨማሪ አቅም መሆን ስለሚችሉ ጥቅሙ የጎላ ነው:: በክልሉ ያሉትን ምቹ የማዘውተርያ ስፍራዎች በመጠቀም በቀጣይ ትልልቅ ውድድሮችን በማካሄድ ተጨማሪ ተሞክሮዎችን ለመውሰድ እና ውጤታማ ተሳትፎ እንዲኖር ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑንም ጨምረው ጠቁመዋል::

## ከዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## ለማህበረሰቡ ደጀን የሆነው ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ

**ዳንኤል ዘነበ**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማኅበረሰቡን ችግር በመለየት የጥናትና ምርምር ስራ ማከናወን ለዘላቂ የሀገር እድገት መረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል። የጥናትና ምርምር ሥራዎች ዋና ግብ የሕዝብን ተግዳሮት መፍታት መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሠሩ ሥራዎችም የሀገርን የእድገት ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ እንዲሁም የማኅበረሰቡን ኑሮ የመቀየር አቅም ያላቸው በማድረግ መሥራት ይኖርባቸዋል።

ይህም ተቋማቱ ከመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደቱ እኩል ለማህበረሰቡ ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሥራ የማከናወን ድርብ ኃላፊነት እንዳለባቸው አመላካች ነው ። በዚህ ረገድ እንደ አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የመማር ማስተማር ሥራውን በይፋ ከጀመረበት 2004 ዓ.ም ጀምሮ ምርምር በማድረግና የማህበረሰብ አገልግሎት በመከወን አንፃር የተሰጠውን ድርብ ኃላፊነት እና ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

ዩኒቨርሲቲው የተቀናጀ የማህበረሰቡን እድገት ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ተግባራት ማለትም በግብርና፣ በሜዲካል /በሕክምና/ ቱሪዝም ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት የሀገሪቱን እድገት ለማጠናከር በሚያግዙ ተግባራት ላይ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ላለፉት ዓመታት በምርምር ዘርፍ የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የምርምር ስራዎችን በማከናወን ረገድ አመርቂ ውጤቶች እየተገኙ መሆናቸው ይታወቃል። በተለይም በግብርናው ዘርፍ የአካባቢውን የልማትና እድገት መንገድ የሚያሳድጉ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው የጥናትና ምርምር ሥራዎች እየሰራ ይገኛል::

በተቋሙ የተሰሩ የግብርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች እና ተዛማጅ ሥራዎች በተጨባጭ የአካባቢውን ማህበረሰቡን ተጠቃሚ በማድረግ የአርሶ አደሩን የኑሮ ደረጃ መቀየር የሚያስችሉ እንደሆኑም ይታመናል።



ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ከሀዲያ ዞን ፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ከተገኙ ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ባደረገበት ወቅት፤

ዩኒቨርሲቲው የማኅበረሰቡን ችግር ለመፍታት የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቋል።

ከሰሞኑ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ከሀዲያ ዞን ፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ከተገኙ ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርጓል። በዚህ መድረኩ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሀብታሙ አበበ እንደገለጹ፤ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ከዕድሜው በላይ በርካታ የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን ብሎም ችግር ፈቺ የምርምር ውጤቶችን እያበረከተ ያለ ተቋም ነው። ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በመማር ማስተማርና ምርምር ሥራዎች ማህበረሰቡን እያገለገለ ይገኛል ብለዋል።

ዶክተር ሀብታሙ፤ ላለፉት ዓመታት በመማር ማስተማርና ምርምር ሥራዎች እንዲሁም በአግሮ-ፕሮሰሲንግና በቴክኖሎጂ ሽግግር ማህበረሰብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ዘርፈ-ብዙ ሥራዎች መሥራታቸውን አስረድተዋል። በተቋሙ ሥር በሚገኙ በሰባቱም የምርምር ማዕከሎች ላይ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ማህበራት የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን፤ በዚህም የአካባቢው ማህበረሰብ ተጠቃሚ መሆን ችሏል። ዩኒቨርሲቲው ጠንካራ የአይሲቲ መሠረተ ልማት ገንብቶ አገልግሎት ላይ ማዋሉን ለፈጠራ ስራዎች እንደሚጠቀም ጠቁመዋል። ተቋሙ የሰላም አምባሳደር በመሆኑ ይህንኑ አጠናክሮ ለመቀጠል የሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘላቂ ድጋፍ ያስፈልጋል ብለዋል።

የሀዲያ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ማቴዎስ አኒዮ በበኩላቸው፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የጀመራቸውን ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን በጋራ እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል። ተቋሙ በሚሳተፍባቸው ዘርፎች ለውጦች መኖራቸውን አመልክተዋል። በዞኑ የተለያዩ አካባቢዎች በዩኒቨርሲቲው የተጀመሩትን መልካም ተግባራት በመደገፍና በአብሮነት በመሥራት ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እንደሚያደርግም ቃል ገብተዋል።

በጥቅሉ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት አግሮ ፕሮሰሲንግ ፣ ሜዲካል ቱሪዝም፣ ታዳሽ ኃይል እና የተቀናጀ የከተማ ልማት ዘርፎችን ለይቶ የህብረተሰቡን ችግር ለመፍታት እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ሲሆን ፤ የማህበረሰብ አቀፍ የበጎች ዝሪያ ማሻሻያ ፕሮግራም አንዱ መሆን ይጠቀሳል። በአካባቢው የበጎች ዝርያ ማሻሻያ ፕሮግራም መጀመሩ አርሶ አደሩ ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኙ የሚያደርጋቸው እንደሚሆን እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የማኅበረሰቡን ችግር ለመፍታት እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የበርካቶች እምነት ነው።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ